
# የብርሃን ፍቅር

ከደበበ ሰይፉ




" . . . ይህ ቅጽ የእስካሁን ድምር የሥነ ግጥም ሙከራዎቼን ሲሶ ያህል የያዘ ነው ። ከእነዚህ ሲሶ ያህሉ ደግሞ ፡ ገሚሶቹ በቅድመ - አብዮት የተጻፉ ናቸው ። ቅድመ - አብዮት የልጅነት ግጥሞቼ ፣ ለድኅረ - አብዮት የጐልማሳ ግጥሞቼ ፣ ባያሌው አበው እንደ መሆናቸው ዐሥራዉ ፣ በጅምላ ልገድፋቸው አልፈለኩም ፤ በድምሩ ልዘላቸው ። ስለዚህም ነው ፣ ኅትመት ፋናወጊ ሁኗቸው ፣ ወደ እናንት ውድ አንባቢዎቼ ስሸኛቸው ፣ ብኩርናቸውን እንደ ጠበቁ እምታገኟቸው . . . "

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋው ብር 2.25

መታሰቢያነቱ

ለአብዮታዊት እናት ሀገር
አንድነት
ለሚታገሉ ሁሉ



# የብርሃን ፍቅር

AL-52/SEY
SoloMosisa

ከደበበ ሰይፉ

ሥነ ግጥም — ቅጽ ፩

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፸

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| እንደ መነሻ | ፯ |
| ሙዚቃ – የምች መድኃኒት | 9 |
| ተስፋ — ጨረቃ | 11 |
| ድንቄም መምህር | 13 |
| ብቸኝነት | 14 |
| ወፊቱ | 15 |
| የሕይወት እጅ | 16 |
| ይርጋ ዓለም | 17 |
| ሰማይና ምድር | 18 |
| ያች ቆንጂት | 20 |
| እማማ. . .እማማዬ | 22 |
| ዳኢቴ (አንዲት የሲዳሞ ሴት) | 26 |
| አዶ ላንቃሞ (አንድ የሲዳሞ ወንድ) | 28 |
| እቴቴ | 31 |
| ላንቺ ለጨለማዋቱ | 33 |
| ልጅነት | 34 |
| ወለምታ | 36 |
| ያባትህ ልጅ | 38 |
| የንፉግ ምፅዋት | 41 |
| አዬ — የኔ ዝምታ ጋግርት | 43 |
| ልጅቱ — የዘመኝችቱ | 44 |
| ስንብት | 46 |
| ፀሐይን ላያይ ተፈጥሞ | 49 |
| ሸር በይበት ሸር | 50 |
| ዘመዴን ስሳመው | 51 |
| አንተን በመሻል አያሳጣኝ | 52 |

ርዕስ ገጽ

አለ ፥ 'ጠና በል' እሚለኝ .................................... 54
እሱ ነው — እሱ .................................... 55
ዛሬን እንኳ ፥ .................................... 59
ብቻ መገኘትሽ .................................... 61
ሐዘንሽ አመመኝ .................................... 62
ለድንገት — በቀል ፈላስማ ዐርበኞች .................................... 64
ቋጥኙ .................................... 66
በትን ፥ ያሻራህን ዘር .................................... 67
ትዝታን ማለስለሻ .................................... 68
ገና በልጅነት .................................... 69
መንታ ነው ፍጥረትሽ .................................... 70
በቀበሮ ጉድጓድ .................................... 71
ጥሬ ጨው .................................... 72
አድማሳዊ ፍቅር .................................... 73
መሰከረም .................................... 74
ፀሰሙ ሠየማት .................................... 84
ምነዋ ባየሁኝ .................................... 86
ጋዜጠኛዉ .................................... 87
ትዝታ — ከበሮ .................................... 89
ፍቅርና ተግባር .................................... 90
አይ ጆኒ — አይ ጆሊ .................................... 92
ያቺን ሚች ቀን .................................... 96
ጉዟችን .................................... 98
እንደግ እንደ ዛፍ .................................... 100

# እንደ መንሻ

ይህ ቅጽ የእስካሁን ድምር የሥነ ግጥም ሙከራዎቼን ሲሶ ያህል የያዘ ነው ። ከእነዚህ ሲሶ ያህሉ ደግሞ ገሚሶቹ በቅድመ - አብዮት የተጻፉ ናቸው ። ቅድመ - አብዮት የልጅነት ግጥሞቼ ፥ ለድኅረ - አብዮት የጉልማሳ ግጥሞቼ ፥ ባያሌው አበው እንደ መሆናቸው ዐሥራዉ ፥ በጅምላ ልገድፋቸው አልፈለኩም ፤ በድምሩ ልዘላቸው ። ስለዚህም ነው ፥ ኅትመት ፋናወጊ ሁኗቸው ወደ እናንት ውድ አንባቢዎቼ ስሸኛቸው ፥ ብኩርናቸውን እንደ ጠበቁ እምታገኟቸው ።

ስለ እኔዉ ግጥሞች እኔው ማሔስ የለብኝም ። እሚገባም አይ መስለኝም ። ይህማ ፥ ሌላው ቢቀር የብርቱ አንባቢዎቼን እስተ ውሎት መጠየቅ ይሆንብኛል ፤ በእሽቅድድም መንጠቅ ። በሌላ ረገድ ፥ ከሒስ መደብ እማይገቡ ጥቂት ነጥቦችን ብወራውር መልካም ይመስለኛል — በተለይም በድግምግሞሽ በግጥሞቼ ውስጥ ስላነሣኋቸው ርእስ ነገሮች ።

የዕድሜዬን ግማሽ ለሚያህል ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተማሪነትና በመምህርነት እንደ መቆየቴ ፤ የምሁራንን ጉዳይ የግ ጥሞቼ ጉዳይ ያደረኩበት ጊዜ ጥቂት አይደለም ። ለምሳሌም ከቅድመ — አብዮት ግጥሞቼ መኻል ፥ "ድንቄም መምህር" ፥ "ጥሬ ጨው" ፥ "ሰማይና ምድር ፥" "እማማ...እማማዬ ፥" እና "ያባትህ ልጅ" የተሰኙት በቀጥታ ምሁር ነክ ጉዳዮችን እሚያወሱ ሆነው ነው ፥ እምታገኟቸው ። በተለይም የመጨረሻዎቹ ሁለት ግጥሞች የወቅቱን የተማረ ትውልድ ሀገርተኛነትና ሕዝባዊነት እሚጠይቁ ናቸው ። በፊውዶ ቡርዧ መስፈራርቾ ሥርዓት መወጣሽቱንና የማንነት መለዮውን መጣሉን እሚያንጐራጉሩ ። ይህ ይሁን አንድነታቸው እንጂ ጉልህ ልዩነትም በመኻላቸው አለ ። "እማማ . . .እማማዬ ፥" ሀገርኛ መለዮውን አጥቶ የነበር ትውልድ የፀፀት እንጉርጉሮ ነው ። በሌላ ገጹም የራስ ግንዛቤ የተሐድሶ መዝሙር ። "ያባትህ ልጅ" ግን ፤ "እንቺ ልጅ ኩሪባቸው በእንግሊዝ አናግሪያቸው" የተሰኙትን ስንኞች የዘፈነውን(ያዘፈ ነውን) ትውልድ ረግረጋማነትን ባንድ ፊት ፤ በሰማየ ሰማያት

"ቋንቋ" ካልሆነ በባላገር ልሣን እንደበታችን አይጨቀይም(ምድራዊ አይሆንም) ይሉ የነበሩትን አንዳንድ የቀደም ሊቃውንት መሠረኅነትን ፀሌላ ሬት ፤— በግንጾር የተወረወረ የታዛቢ ቁጣ ነው ፤ ፀትር ። በተረፈ ፀሁለቱም የሀገርተኝነትና የሕዝባዊነት ድምፆች ቢሰሙም ፤ በመጀመርያው ሀገርተኝነት ነው ይበልጥ እሚጐላው ። በሁለተኛው ደግሞ ሕዝባዊነት ።

ይኸው ጉዳይ በድኅረ አብዮት ግጥሞቼም ውስጥ መዛመቱና እንደገና መከሠቱ አልቀረም ። ምሳሌ ቢያስፈልግ "ሐዘንሽ አመመኝ" ንና "ልድንገት — በቀል ፈላስማ ፀርበኞች" የተሰኙትን መጥቀስ ይቻላል ።

"ሐዘንሽ አመመኝ ፤" እንደ "እማማ. . .እማማዬ ፤" ሁሉ ከተማረው ትውልድ መኻል በሥጋም በመንፈስም ከሀገሩ ርቆ የነበር ወገን እሚያሰማው የቅሬታ እንጉርጉሮ ነው ። የብክነት ፀይነጥላው ተገፎለት ራሱንና ሀገሩን ማተኮር ሲጀምር ከውስጡ እሚብሰከሰክ የንፍሱ ጩኸት ነው—የናፍቆት ፤ የፀፀት እሮሮው ። በሌላ በኩል ግን ፤ በሱና በየሱነቱ (ማለት በሀገሩ) መኻል የቆመውን ማንኛውንም ገደል አፈራርሶ ፤ እሱነቱን (የእሱነት መለዮውን) የመፈለግና የማግኘት ቁርጠኝነቱ እሚሰማበት የብሩህ ተስፋው መዝሙርም ነው ።

እርግጥ ነው ፤ "ሐዘንሽ አመመኝ ፤" እጅግ አያሌ ኢትዮጵያውያን በረኃብ በሚረግፉበት ወቅት የተጻፈ እንደ መሆኑ ፤ ከሌላኛው ግጥም ይበልጥ ስሜትን ሊጫን ይችላል ፤ ሊያም ። ሁኖም ፤ ብሥራት ፍጹም የተለየው አይደለም ፤ ውጋጋን ። ቀቢፀ — ተስፋ ያደቀቀው ትውልድ ድምፅም አይደለም ፤ ክቶም ።

ሁለቱም ግጥሞች የተማረው ትውልድ ፀይን ላይ ወድቆ የነበረውን መንታ ጭምብል ያሳያሉ ። ማሳየት ብቻም ሳይሆን ጭምብሉ በተራው ሲወድቅ ፤ ትውልዱ ወደ እውነታው እውነት ለመቅረብ መብቃቱንም ያበሥራሉ ። በ"እማማ. . .እማማዬ ፤" ሀገሩን ባዶ ማጀት አድርጐ ይገምት የነበረው ትውልድ ፤ ቆይቶ መልካም ገጽታዋን ያያል ። በ"ሐዘንሽ አመመኝ ፤" ሀገሩ ሁሉ በጅዋ ሁሉ በደጅዋ ትመስለው የነበረው ትውልድ ፤ የሚያስበውን



ያህል እንደሌላት ያስተውላል ። ዋናው ቁም ነገር ፤ ሁለቱም ከጽንፋዊ አተያዮች ተነሥተው እሚደርሱበት ግብ አንድ መሆኑ ነው ። ከራስ ጋር — ከሀገር ጋር ዕርቅ ። ይህም የግጥሞቹ እንጉርጉሮነት ሳይሆን መዝሙርነት ይበልጥ ጐልቶ እንዲሰማ አድርጓል ።

በሌላ ረገድ ፤ "ያባትህ ልጅ" እና "ድንገት — በቀል ፈላስማ ዐርበኞች" እሚመሳሰሉበት ነጥብ አለ ፤ እሚናጾሩበትም ። ሁለቱም ከተማረው ዘመናዊ ትውልድ መኻል አንዳንዱን እሚያስታዝቡ ናቸው ፤ ሕዝባዊነቱን እሚጠይቁ ። ይህም ሁኖ ፤ "ያባትህ ልጅ" ዕውቀቱን በአንደበቱ — አፍርንጅ ከብዙኃን እንዳይደርስ ያደረገውን ምሁር በስላቅ የሚሸነቁጥ ሲሆን ፤ "ድንገት — በቀል ፈላስማ ዐርበኞች" ደግሞ ፤ በተለይ ከ1966 መጋቢት እስከ ሰኔ በነበረው ጊዜ ከሥልጣን ርካብ ተንጠላጥሎ ከብዙኃኑ ሕዝብ ላይ ሊፈናጠጥ ከጅሎ የነበረውን እንደቡቱ ነቀልቃል ምሁር ይሞግት ሲባል የተጻፈ ነው ፤ ያጋልጥ ። ህሊናውን ይውቀስ ሲባል የተወረወረ ነው ፤ ይቆንጥጥ ።

በተረፈ (እሚዳበሉበት ወቅት መኖሩን ሳንዘነጋ) ፤ ቅድመ አብዮት ግጥሞቼ በጣሙን በግለሰባዊ ገጠመኞች ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ፤ በዛ ያሉት ድኅረ — አብዮት ግጥሞቼ ግን በሀገራዊ ገጠመኞች መነሻና ምክንያት የተጻፉ ናቸው ። ከሁለቱም በኩል ካሉት መኻል በሙገናኛ — ብዙኃን የተሰሙ አሉ ። በመጽሐፍ ጥራዝ መገኘታቸው ደግሞ በቅርብና በድግምግሞሽ ለማጤን ያስችላል ።

በያንዳንዱ ግጥም ግርጌ የተጻፈበት ዓመተ ምሕረት ሠፍሯል ። በግጥሙና በተጻፈበት ወቅት አንዳች ጥብቅ ዝምድና ቢኖርም ወራት ታክለዋል ። አንዳንድ መግለጫዎችም እንዲሁ።

ደበበ ሰይፉ

መስከረም — ፲፱፻፸፱

# ሙዚቃ — የምች መድኃኒት

ያለፈው ይመጣል
የሞተው ይነግል ።
እስቲ እህህ በሉ
በሉ እስቲ አንጐራጉሩ
የዘመድ የወዳጅ ይፈንቀል መቃብሩ
ይሰበር ሣጥኑ
ይገለጥ ከፈኑ
የምጽዓት እምቢልታ ዋሽንት ነጋሪቱ
ይሰማው ልባችሁን ቀርኑ መለከቱ ።

ዐይን ዐይቶት ያለፈው
ልብ የመዘገበው
ሠራዊቱ ይንጋጋ የቅርብም የሩቅ
በሙዚቃ ሥዕል ይነደፍ ይድመቅ ።

"ዋ ! አለ አሞራ ፣
ዋ. . . .አለ
እጅዋን ሊበላ
ዋ. . .አለ
ዐይኗን ሊበላ
ዋ. . .አለ
ዋ. ..አለ አሞራ
ዋ. . .አለ ።"

ትካዜ ለቅሶዬ
ልቤ መባባቱ
ላንጐራጉር ብዬ
ዐይኔ መሟሟቱ ።
ስትሠርፅ ሙዚቃ ትንሣኤን ደውላ
ከምድር ከሰማይ ፤
ሙታን እንዲነሡ ያልታየው እንዲታይ
ብትጣቀስ ከእንባ ብታመጣም ብካይ ፤

የዳዊት በገና ጉንጨን ብታቀላ
ሳኦላዊ ነብሴን ቁስሌን አድን ብላ
ሸክሜን አቀል ብላ ።
በዘመናት አረም ተውጦ የቀረውን
በዝንጋዔ ደለል የተዳፈነውን
ዛሬ የመከሠቱ የጿ ቢሆን ጥፋቱ
መቼ ይርቃትና ከቶ አብነቱ?

ስንቶቹን አየሁኝ አንች የነብስ ነብስ
ሕይወትን ሲቀምሱ በአንቺው ምላስ
ጉህና ቃና ሁሉ አንችጋ ሲደርስ
ጣዕመ መልካም ነው ምግበ መንፈስ ።
ይሁንም እ/ችዬ !
ብርታቱ ይከዳኛል
ለአንቺው መሥጋቴን መደበቅ ምን ያሻል?
ከቶ እንዳትተይኝ መዐቴ ከብዶሽ
ያለብኝን ጭንቁን
ምሬቱን ሐዘኑን
እንዴት ላዋይሽ?
ይህም ሁሉ ሁኖ ፤
እየተጠራጠርኩ ማመኔም አልቀረ
ታዳጊዬ እንደ ሆንሽ ከኔ አልተሠወረ ።

በይ እንግዲህ በርቺ
የትላንቴን እንቺ
የጭንቅ ግማሽ ፤
በይ እንግዲህ በርቺ
የዛሬዬም ላንቺ
የእንባዬ ፅላሽ ።
እንዲህ ካልተራዱ ካንቺ ብጤዎቹ
አጣድፎ ይገድላል የሕይወት ፀሐይ ምቹ ።

---

.1960



## ተስፋ—ጨረቃ

አታውቅና መቼም
ሁልጊዜም መሸለም
ሁልጊዜም መሸም ፤
ሕይወት አዱኛዋን
የውሰት ዕቃዋን
ፍሥሐ ሲሳዬዋን
ክብሯን ማዕረጓን ፤
መልሳ ወሰደች ።
ሳይቀር ወዳጆቹን
ከጉኑ አራቀች ።
እሱም መደነቁ
በመልኳ አበባዙ
ካባዋ መሞቁ
ውርጯ መቀዝቀዙ ።

ተመኝ ቢጨንቀው
የሚያዘንበው እንባ ፤
ጉርፍ ሁኖ ቢያደርሰው
ካለመኖር አምባ ።
ዘመድ መኻል ሁኖ
የሚያዋየው አጥቶ
ወዳጅ መኻል ሁኖ
የሚጠራው ጠፍቶ
የነበረው ደርቆ
በአለው ግን ሲኖኝ
ጮኸ ራሱን አንቆ ፤
‘ም/ም አልቀረኝ
ሞቴን ለግሰኝ!’

ታዲያ ካፉ አይዘልቅም
ይህ ተስፋ መቁረጡ

አለ ሴላ ዓለም
ዘልቆ ሲታይ ውስጡ ።
እሰው ፊት ነው የወቃው
የእንባዉን አዝመራ ፤
እሰው ፊት ነው ያለው ፣
'ተስፋ ቢስ ነኝ እኔ
ዕድለ ሰባራ !'
ግን በስውር ጣቶችህ ብትደባብሰው
በሕሊና ኤክስሬይ ብትመረምረው ፣
ከዛ ብረትማ ውርጭ የልቡ ሳንቃ
ተቆፋን ታገኛለህ የሙጥኝ ተጣብቃ !
እንዲያ የጨለመውን
    ጽልመት የሆድ ዕቃ ፣
የምታበራዋን
    ትጉኋን ጨረቃ ።

* * *

.1961



## ድንቄም መምህር

ራሱን ሲክሽን
ሲያንቆለጳጵሰው
ማር—ወተት ሲያረገው
ከንፈሩን ሲስመው
    ሊያስተምረኝ መጥቶ ፤
    ብሽቅ አደረገኝ
የተረብ ጋዘና መሆኑ ሰቀቀኝ ።
ለጋ ጊዜዬ ላይ መሸናቱ ነደደኝ ።
እንዳይሰማው ፈርቶ
ልቤ አንሾካሾከ ፤
"አስተምረኝ ባለ
  ስንት ነገር አለ !"

* * *

.1962

## ብቸኝነት

ጹትማው ተይዞ ሲጣል ምድረበዳ
ሰው ጹራሱ በቀር ለሌላው እንግዳ
ሁሞ ሲውል ሲያድር በብቸኝነቱ
'ሞተች!' ይላል ዓለም
ውስጣዊ ፍጥረቱ ።

* * *

1962



## ወፌቱ

የኀዋውን መንገድ እንዳሻሽ ስታገር
ሳትገጪ ፣ ሳትገጭ በግብር ሳትያገር
ተራራ ጫፍ ሁነሽ ተራራ ስታይ
አድማስ ሳይወስንሽ የትም የት ስትዘይ ፤
እረ ምን መለሰሽ ?
ወደኋላ ያዘሽ ?
መሸት ከማለቱ ያደነቃቀፈሽ ?
ወፌቱ በሌሊት ምን ይሆን ታስቢ
እኔን መስልሽኝ ጐጆሽ ስትገቢ ።

* * *

.1962

# የሕይወት እጅ

ሚዳቋ የሚያባርር ነብር ሁኚ
ጨረቃን የሚያሳድድ ሕፃን ሁኚ
ልብረር ስል
ልብነን ፥ ከጥላዬ ፈጥኚ ፤
              መለሰኝ ።
ያንተ አይደለችም አለኝ ።

ማግ ሲተናነቀኝ
    እየኮረኮረኝ ።
ሲያስገለፍጠኝ
    እየቆነጠጠኝ ።

* * *

.1963



# ይርጋ ዓለም

ይርጋ ዓለም
ዋ. . . .ይርጋ - ለም
የልጅነቴ ሕልም ቀለም
ዐይኔን የከፈትሽው ጨረር
ወርቅማይቱ ጀንበር ።

ዕፅዋት ፥ ሥራሥር ፥ ፍራፍሬ
ዶቅማ ፥ ጐዶሬ ፥ እንጆሬ ፤...
የቅጠል እንግዳ የኩልቤት ፥
እንሰት ቡና ፥ ቡና እንሰት
    ሲያለብስሽ ሲያከናንብሽ
    ሲሞሽርሽ ሲያደምቅሽ
      ሳያከብርሽ ፤
    ካባውን ሲያጠልቅልሽ
      ሳይሾምሽ ፤
ዛሬ ባስተውል ታዘብኩሽ ።

የተፈጥሮ እምቢልታ ጥሩንባ
አረንጓዴ ቢጮህ ባንች አምባ
ማንስ ነቅቶ ፥ ኧሀ ሊልሽ ?
ማንስ በቅቶ ፥ ሊታደግሽ ?
ናፍቀሽኝ እንደ ገሠገሥኩ
አጠገብሽ በደረስኩ
ጭቃ. . . .ኮረት
ፍራሽ. . . .ዝገት
    ሁነሽ ሳገኝ
    ምን ይዋጠኝ ?

አባ ወራው እንደ ሞተበት
ወራሽ እንዳለማበት
      ገሬ ቤት ፥
ሲያይ ልትዘነጣጠይ
እሚጠግንሽ ጠፋ ወይ ?

ሰዎችሽ ሸሹን ፥ ሔዱን ?
ወደ ደራበት አመሩን ?
እንደ አሮጌ ጨርቅ ሲጥሉሽ
ማን ይጠቃቅምሽ አሉሽ ?
ብቅሬታ ታዘብኩሽ ።

አንቺ ብቻ የማትቀልጪ
በሳብ በወዝ የማትበልጪ ፥
ለምን ?
ድጅና መዶሻ አካፋ
ጠረኑስ ካንቺ የጠፋ ፥
ለምን ?
ባጥቢያሽ የገደል ማሚቶ መተኛቷ
በቦዘን ምክንያት መደፋቷ ፥
ለምን ?.....እኮ ለምን ?
ምፅዓትሽ አይቆጠር
አልሞትሽም እሚሉ ነገር ።
አለሽ እያሉ ሲቀብሩሽ
ብቅሬታ ታዘብኩሽ ።

ግዶለሽም ፥ ብሶትሽን አትደብቂ
ጉልበትሽን አበራቺ ፥ አነቃቂ
ፍቅርን በወዝሽ ሰንቂ ።
እንዳሽለብሽ እንዳትቀሪ
ነቃ ማለቱን ድፈሪ ።
ዕፅዋቱን ተመርኩዘሽ
ተነሽ....እባክሽ ተነሽ ፤....
ይርጋ ዓለም
ዋ.......ይርጋለም
የልጅነቴ ሕልም ቀለም
ዐይኔን የከፈትሽው ጨረር
ወርቅማይቱ ጀንበር ።

---

.1964



## ስማይና ምድር

በጀርባዬ ተንጋልዬ ፥
እውዬ
አፍላጦንን ከራስጌዬ ፤
ሔዶ ሰማዩን ቀዶ ሕሲናዬ ።
በቅጽበት የፈተልኩትን ለብሼ
ሞቆኝ ፤
በኔው ዓለም እኔው ነግሼ
ደልቶኝ ፤
ከጽድቁ ገቢታ ቀምሼ
ጣፍጦኝ ፤
ቀና ብል ፤
ያቻት ጉጆዬ ደብዝዛ
እንደ ክፉ ቀን ቀዝቅዛ ፤
ንፉግ ፍቅሯን ለማየቱ
ብርሃን እንኳን መታጣቱ ።

* * *

---

.1964

## ያች ቆንጂት

ያቺ ቆንጂት ትመጣለች
እያዜመች
እማማዋ ሲወጡ
ቡና ሊጠጡ ።
"ጋሼ ላጫውትህ ?" ትለኛለች
ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
"እሺ ቆንጅትዬ" እላታለሁ
መጻሕፍቴን እየገፋሁ ።
ትጫወታለች
የባጥ የቆጡን ታወራለች
ቆንጂትዬ ፣ ዐይናማዋ ቆንጂትዬ
ጥርሷን ፍልቅቅ እያደረገች
ከንፈሯን እያፋተገች
ትንከተከታለች ፤
(ግን ድንገት ልታቋርጠው
ስሜቷን አንዳች እንደሚገስፀው)
"ምነው ቆንጂትዬ ?'
"ምንም አይደል ጋሼዬ"
ብር ብላ ትሔዳለች
ብር ብላ ትመጣለች
ፊደሏን በጅዋ ጨብጣ ፤
(ዐይን ጥላ ነበረባት
ትምህርት እሚከለክላት)
"አታስተምረኝም ?" ትለኛለች
ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
"እሺ ቆንጂትዬ" እላታልሁ
መጻሕፍቴን እየገፋሁ ።
እጠገቤ ትቆማለች
ቆንጂትዬ
ስንጥሯን እንደ ጠቆመች



ጣቴን ያዝንጂ እያለች ።
ይዛትና
ጠጋ አድርጌ አቅፋትና
ሀ—በይ ስላት
ሁ—በይ ስላት
እቆይና
የጣቷ ሳብ ሲያዳልጠኝ
'በ' ን ጠንቁላ 'ቀ' ስትለኝ
አያትና
ድምፅዋ ሲደክም እሰማና ፤
"ምነው ቆንጅትዬ ?"
"ምንም አይደል ጋሼዬ"
ብር ብላ ትሔዳለች
ቆንጂትዬ
እንደገና ልትመጣ ፤
(አፍታ ሳትቆይ
ነጠላዋን ቆንጥጣ)
"እንደ እማዬ አታለብሰኝም ?" ትለኛለች
ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
'ነይ ላልብስሽ' እላታለሁ
መጻሕፍቴን እየገፋሁ ።
አለብሳት ስል አይስማማት
አንዴ ሲያጥር ሲረዝምባት
ግራ ገባኝ
ግራ ገባት ።
ፈርዶብኝ
ፈርዶባት ።
ብር ብላ ሔደች ቆንጂት
በማግሥቱ እኅቴ ናት
ነጠላዋን የሰጠቻት ።

---

.1964

# እማማ...እማማዬ

እማማ እማማዬ...
የኔነት መደብ መብቀያዬ
የኔነት ቀለም ንሻራዬ ፤
እስቲ ፡ እንምከር እነወያይ
ገበናሽ ገበናዬ
ተፈልቅቆ እየታዬ ።

ከማሕፀንሽ እምባ በቅዬ
መልክ ስምሽን ከመልክ ከስሜ አንጠልጥዬ
ግርማ ሞገስሽን ተካፍዬ
          ያለውለታዬ ፤
ሰሐሽን ተቀብዬ
     ያልዕዳዬ ፤
ዕድልሽ ከዕድሌ ተቀራኝቶ
ገነቴ በገነትሽ ተመሥርቶ
ቍዳዬም ከፍዳሽ ተጋርቶ ፤
ምነው ታድያን ቀይቶ ይታየኝ ጀመር ተለያይቶ
ያዋደደን ገመድ ተፈቶ
ውጥሩ ረግቦና ላልቶ ?
ምንድን ሆነ እማምዬ ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፥ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፥ በማኻላችን ምን ነፈሰ ?

ብትጠሪኝ እንዳልመልስሽ
ብትልኪኝ እንዳልላክሽ
ፊቴን አዙሬ እንዳልፍሽ
ብትቀርቢኝ እንድርቅሽ
ብታወራ እንዳላደምጥሽ
ብትጽፊ እንዳላነብሽ
ውሸት ብዬ እንድሥቅብሽ
ቍረት ብዬ እንዳገጥብሽ



ያደረገ ፥ ምንድን መዓት ተተኮሰ
ምንድን ሆነ እማምዬ ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ ?
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፥ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ ?

እባክሽ ፥ ዘራችን በውል ይታወቅ
በወግ ይቆጠር አይደበቅ
በመጤ ተረብ አይታመቅ
በባዕዳን ክርን አይድቀቅ ፤
እኔና አንቺን እሚያውቀን
የታሪክ ልሣን ይፍረደን ፥
ሲይዙኝ በጠይምነቴ
ፀሐይዋ አትሁን ምክንያቴ ።

እማማዬ ፥
ከዶቃው ጋር ከአፈሩ
ከዳዶው ጋር ከእሾሩሩ
ከሕመሙ ከጭንቀቱ
ከቡረቃው ከሐሴቱ
ከበጋው ጋር ከክረምቱ
ከብርዱ ጋር ከሙቀቱ
የነበርሽ—የተካፈልሽ ፥
አሁን ወዴት ይሆን ያለሽ ?
   በይ ፥ አምባሽ የለሽም ወይ ዳቦ
ጨጨብሳ የልሽም ወይ ጭኮ
ጕመን ፡ የለሽም ወይ ክትፎ
ቆሎ የለሽም ወይ ገንፎ ፤
ያንቺን ገበታ ደፍቼ
ጽዋሽን በእጆቼ አንክቼ
   የባዕድ ማዕድ ስመጥን
   ወጥሽ ሻግቶ ይደፋን ? ይደፋን ?
         ጠላሽ ሾምጥሮ ይፍዕስን ? ይፍዕስን ?
ብፊራ ነው በሰው ምላስ
ቃናሽ ኋላ እንዳይዳስ ፤

ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው
ብፈራ ነው እማምዬ ብጨነቅ ነው ።
የሕይወትሽ ማኅደር ብራና
እንዳያዘ ያንቺን ዜና
ሳይገለጥ ቀን ያልፍና
ሳይነበብ ሳይወራ ይቀርና ፤
እንዳይደድቡ ዐይኖቼ
ልብ ሕሊና ጆሮቼ
የሕያው ገጽሽ ውበቱ
እንዳይነጣ ደም ግባቱ
ዐመዱ እንዳይቀር ዐለቱ
ኮረቱ እንዳይቀር ሐውልቱ ።
ብፈራ ነው እማምዬ ፣ ብጨነቅ ነው
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው ።

ካንቺ ርቄ—ከእኔ ርቄ
ከየምናምኑ ወድቄ
በሌላው ዕድር ጠልቄ
ልናገር ብል — ማን ሊሰማኝ?
ልጎብዝ ብል — ማን ሊያኮራኝ?
እባክሽን ፣ አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፣ ፍቅርሽን ገና አላወኩም ።
በአርአያሽ መፈጠሬን
በፈለግሽ መወሰኔን
መወለዴን ባንቺ ልደት
መቦረቄን ባንች ልጅነት
መፈንደቄን ባንች ተረት ፤
—እንደምሞትም ያንቺን ሞት—
አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፣ ፍቅርሽን ገና አላወኩም ።

እማማ እማማዬ ፣
የእኔነት መደብ መብቀያዬ



የኔው ቀለም አሻራዬ ፣
ነብሴን ልጣል ፤ ካንቺው ጉያ — ካንቺው ገላ
ዳግም ከቶም አልሁንብሽ ተቀጥላ
የወግ ልጅ የይስሙላ ።...
ቃል ኪዳኔን ተቀበይኝ
የኔ ሁኚ ፣ ያንቺ አድርጊኝ
አልለይሽ ፣ አትለይኝ—
አይበድሉም ብበድልሽ
መቼም የትም እናቴ ነሽ ... እናቴ ነሽ ።

* * *

---

.1964

እናት ሀገርን "በድለንሽ ነበር ፣ ይቅር በይን" ማለትን ለሚደፍሩ ወገኖች ።

## ዳኢቴ (አንዲት የሲዳሞ ሴት)

መላ ሰውነቴ እያነባ
ነብሴ ሳትቀር ተንገብግባ
ፀፀሐይ ፀሐይ
ይርጋዓለም ከቀትር ላይ ፤
ዝዬ እንዳልወድቅ
እርምጃዬን ሳጠብቅ ፤
እፏፉውን እየጫረች
በጣቶቿ
በጥፍሮቿ
ሸንኮራውን እየፈጀች
ልጣጩ ሳይቀር እየመጠጠች
እያገላበጠች ፤
ትጓዛለች
ዳኢቴ . . . ትሔዳለች
ፊት ፊቴ ትነጉዳለች ።. . .
(ከገበያ መልስ
የኑሮ ምሱን ለማድረስ)
ሹርባዋ በቀጭኑ ተሠርቶ
የቅቤ ያለህ ከሚል አቧራ ተገናኝቶ
የቆዳ ግልድሟ እየተንኮሻኮሸ
ፍርጥም ያለው ጭኗን እያሻሸ
ትሔዳለች
ትነጉዳለች ።. . .
ጥብቆዋ እንደ ሸሚዝ ያጠለቀቻት
እንዴት ነው የምታምርባት ?
ዶርዶሮነቷ እየተንጨፈጨፈ
ገላዋን
ኤመስ ኦመስ የቱዶረገ
ቡናማ ቀለሟን
እያርከፈከፈ ፤
ጨሌዋን ደሞ ዶቃዋን



ያስጌጠችፀትን አንገቷን
እያበሰባት
ቅቤውን እየከለለሰባት ፤
እያየኋት . . .እያየኋት
ታሳዝነኛለች ዳኢቴ ፤
ገና ብዙ. . .ብዙ ብዙ ትጓዛለች
ፀፀሐይ ፀሐይ
ይርጋለም
ከቀትር ላይ

* * *

---

.1964

## አዴ ላንቃሞ (አንድ የሲዳሞ ወንድ)

ብርማይቱ ጨረቃ
የብርሃን ጠበል አፍልቃ
ተፈጥሮን ስታጠምቃት
እንደገና ስትወልዳት
ነፋሱ ፀቀስታ
በበረዶ እጁ ሲማታ ፤
አዴ ላንቃሞ
ጦሩን ከጐኑ አጋድሞ
ያስተውላል እንደ ነገሩ
አሽቆልቁሎ ከሥሩ
እንደ ዘበኛ
አፈርማታ የቆመበቱን
የእንሰት ።

ጭስ ይጨሳል ዐልፎ ዐልፎ
ለአዴ ላንቃሞ
እየተዳፈነ ነው ቀቄሎ ፤
በቅቤ የጠገበውን
ቡልኮውን
ገለጥ እንደ ማድረግ ብሎ
ሆዱን ሊያሻሸው
እንዲርበው
መልሶ ተወው
ብርድ ነክስ ቢያደርገው ።

ከዛም ታየው... ታየው ባእምሮው
እንደ ደግ ሕልም ደስ ደስ እያለው
ሦስቱም ሚስቶቹ ሲርመጠመጡ
የሱን ጐርሮ ሊያጣፍጡ ።
በልቡ አደመጠ ሲመታ
የያንዳንዷ ልብ ድርብ ድርብ
ሽቅብ ሽቅብ



በ"እኔጋ ነው የሚያድር ዛሬ ማታ" ።
አዴ ላንቃሞ
የዘወትር ጭምቱ
ቀልድ ቀልድ ሲለው ብልሃቱ
(ከዐልፎ ፀልፎ አንድ ዕለት
እየከፋ እንደ መዝናናት )
ወደ ጐጆአቸው ተጉዞ
ሚስቶቹን ይመጣል አዞ ፤
"እራት እንዲበስልልኝ
አዳሬን እመጣለሁኝ ።"

ታዲያ እንዲህ እንደ ዛሬው
ብርማይቱ ጨረቃ
የብርሃን ጠበል አፍልቃ
ቀፈጥሮን ስታጠምቃት
እንደገና ስትወልዳት
ነፋሱ ፀቀስታ
በበረዶ እጁ ሲማታ ፤
ካፋፏ ላይ ቂጭ ብሎ
ጭሱ ሲወጣ ተጥመልምሎ
እያየ ፤ ፈገግ ፈገግ ይላል
ከት ከት ብሎ ይሥቃል
ወንድ የመሆንን ጽድቅ ይከባል
ያደንቃል ።
ደሞም ይፈልጋል
ማወቅ ማረጋገጥ
መግኖ እንደ ሰጠው
ምኔም እንዳይነፍገው ፤
ለእያንዳንዷ ሰዓት
በያንዳንዷ ሌሊት
ሦስት ሴት ከሦስት ራት ።

እግራቸውን ታጥበው
በቅቤ ተሻሽተው
በጢልቱ ቆሙውን

ፀሙሙ ወተቱን
    እሳምረው—አምረው
ሲጠብቁት ሲያውቀው
ሥዕቱንም አፍቅሮ
ግን እንዲጋ አድሮ
ባንድ ራት — ባንዲት ሴት
ተሰልባ ያች ሴት
ሌላው ሳያገኘው
ግን እንደ ተመኘው
ማደሩ ትዝ ሲለው
መብቱ እየተሰማው ፤

እንዲሀ እንደ ዛሬው
ብርማይቱ ጨረቃ
የብርሃን ጠበል አፍልቃ
ተፈጥሮን ስታጠምቃት
እንደገና ስትወልዳት
    ነፋሱ በቀስታ
    በፀረዶ እጁ ሲማታ ፤
ካፋፏ ላይ ቁጭ ብሎ
ጭሱ ሲወጣ ተጥመልምሎ
እያየ ፥ ፈገግ ፈገግ ይላል
ከት ከት ብሎ ይሥቃል
ወንድ የመሆንን ጽድቅ ይከባል
                ያደንቃል ።

እንዲህ እንደ ዛሬው ሞቅ ሲለው ልቡ
ይማከለት ይሆን ያቀደው በቅርቡ ?
አንዲት ጉጂ ነገር ጥቂት ቀን ሸፋሽፎ
አንዲት ጊደር ብጤ ገዝቶ ወይም ዘርፎ
እራት ከአራት እርጎ መብቱን ማጉልበቱ
        ቀልዱን ማፋፋቱ ?!

---

.1964



# እቴቴ

ድሮ ነው ፊት
ፀልጅነቴ ሰዓት ፤
ቀራሩሬ ከማበርበት ቦታ
        መጥታ
ትጠራኝ ነበር ያች እቴቴ
        የጉረቤቴ ፤
"ቡጡና ፥ ወንዝ እንውረድ
ሸንኮራ ቀርጨልህ እንድትጎምድ . . . "
"እሺ እቴትዬ" ብዬ
ጣሳውን ከእጅዋ ተቀብዬ
እከተላታለሁ ወንዝ እቴቴን
        እቴቴን— የጉረቤቴን ።

ውሃውን
ፀሐይዋ ስታፀኸየው
በወርቅ መርገፏ ስታጌጠው
እቴቴም
ጨርቋን ስታንጨፈጭፈው
ስታሽ ስትጠመዝዘው
ስትዘረጋ ስትቀለብሰው ፤
ደሞም ስትዘፋፍነው
"የኔ ቤት እቆላ ያንተ ቤት አፋፉ
ልቤን አመጡልህ እየደጋገፉ"
    ስትለው. . .ስትለው
ትንሹን ልቤን እንዴት ነበር ደስ የሚለው
                ደስ የሚለው ?

ታድያ አፍታም ሳትቆይ እቴቴ
        እቴቴ የጉረቤቴ
ዘረረረረር አድርጋ ልብሷን
ውሃ ውሃ እሚል ጨርቋን
ሣሩ ላይ ጉቶውም ላይ
በየቅርንጫፉም ላይ ፥

ትለኛለች እኔን
እኔን ትንሹ ቡጩን
ውሃው ውስጥ የምንቦራጨቀውን ፤
"እስቲ ደሞ ቀራዬን
እኔ ልታጠብ ገላዬን
አፋፏ ላይ ቁምልኝ
መንገድ መንገዱን እይልኝ
ሰው አለመምጣቱን ጠብቅልኝ . . "
እሺ ብዬ ዲዲዲዲ ወዳፋፏ
እሷም ፈታ ፈታ መቀነቷን
ገልመጥ ገልመጥ ዙሪያዋን
ፍትት ፍትት ፍትትትት ሻሿን
ግልብ ግፍፍ ውልቅልቅልቅ ቀሚሷን
ሙልጭልጭልጭ ውስጥ ልብሷን
ብቅ ጥልቅ ብቅ ጥልቅ ራቁቷን ፤
እኔም ዐየት—ዐየት መንገዱን
ገረፍ ገረፍ—ደሞ ገረፍ ወንዙን
እቴትዮ ዕርቃኗን የምትንቦራጨቅበቱን ፤
ጸጉሯን ወደኋላዋ እየሳበች እየገ—ተተች
ጡቶቿን ለፀሐይዋ እየሰጠች እየለጠጠች
ኋላዋንም ነካ ነካ —ነካ እያደረገች
ስትጫወት እያሾለቅሁ አየት . . .አየት
ደሞ መንገዱንም መልከት. . .መልከት ፤...
ታድያን ዛሬ በጉርምስና ዘመኔ
ያ የጥንቱ ትይታ ተመልሶ መጣ ካይኔ
የረሳኋት እቴቴ
ብቅ ትልብኝ ጀመር ከፊቴ ፤. . . .
ወንዙ ውስጥ ስትንቦራጨቅ
ጸጉሯን ወደ ኋላዋ እየሳበች እየገ—ተተች
ጡቷን ለፀሐይዋ እየሰጠች እየለጠጠች
ኋላዋንም ነካ ነካ—ነካ እያደረገች ፤...

.1964



# ላንቺ ለጨለማዋቱ

ፀሐይዋ ሳትወጣ
በድቅድቅ ጨለማ
ፈልጊኝ
ታገኚኝማለሽ ፤
መልኬ ባይታይሽ
በጣቶችሽ ዳሰሺ
ጠረኔን አሽተሽ ፤
ሌቱ ከነጋማ
እኔም ያንቺ አይደለሁ
አንቺም የኔ አይደለሽ ።

* * *

.1964

## ልጅነት

ጊዜ በጊዜ ቀለበት
ሰተት ።
አይ ያች የዘመን እምባ
በብይ ድብደባ
በኳስ ጥብጠባ
ባውጥ ለቀማ
ተጣባ ፤
ደሞ ትንሽ ተገን ለአበባ
በጉርምስና ፍሬ እምታነባ ።
ቢራቢሮ ማባረር ማባረር
ከቀልም ቀለም መሽከርከር
ለማሳደር
ለከርሞ
አባ ጨጓሬ መሰል ነገር ።

መች ጠፉችሁ
ጓደኞቼ
ካባ አልባሾቼ
እንደ ገዛኝ የልጅነት ሥልጣናችሁ ?

የሕፃንነት ጥኝነት
የዐዋቂ ብልጠት
ዙሪያ ቀለበት
የሕይወት ጉዞት ።
ቋታችሁን ለመሙላት
ሥጋት
ሥፍር—እችሁን ለመመጠን
ብከን ፤
ዳገት—በረዶ መቧጠጥ
መፍረጥ
ጋት ለመቆንጠጥ ።
በዛን የልጅነት መከሊት
ዛሬም እንነግድበት



ብቻ እንሶ ሲመነዘር
መንፈራፈር
ልብን በሲቃ ማንጫረር ፤
መንገድ ብቻ—እግር ሳይኖር ፤
መዳከር
በልብ ጫማ መውተርተር ።
ላለመለምለም መብቀል
ላለማፍራት መተከል ፤
ተስፋ ቅርስ
ምኞት —ውርስ
በግብረ—ጠል
እስቲል ከንበል ።

እልፉ አሜጋ የሕይወት
ልጅነት
ሲያረጁ ሲያፈጁ
ከደጁ
ከልጅ ልጁ ።
ዞሮ ዞሮ ከልጅነት
ኑሮ ኑሮ ከመሬት
እንደ ማለት ።

ጊዜ በጊዜ ቀለበት
ሰተት
አይ ያች የዘመን እምባ
በብይ ድብደባ
በኳስ ጥብጠባ
ባውጥ ለቀማ
ተጣባ ፤
ደግሞ ትንሽ ተገን ለአበባ
በጉርምስና ፍሬ እምታነባ ።

---

.1964
በልጅነት ለምለም መስክ ላይ ልጅነትን ለተካፈሉን ጓደኞቼ።

## ወለምታ (የወዳጅነት አባዜ)

አይጥሩ እንጂ አይውጣ ከእጃችን
ያለዐዋይ እስካልቀረ ሙዳያችን
ወዳጅነት — እሚያሰናስል ሀብላችን፤
መዳቡ አልማዝ አፈሩ ወርቅ
የነብስ ብርቅ የሥጋ ድንቃድንቅ ፤
እብስ ሲልም ድንገት ፣ የፍቅር ሌባ ልሶት
እግዚኦታ አይመልሰው ፤ ጾም ወይ ጸሎት ።
ሩቅ አድማስ
በዐይን አይላስ ፤
አእምሮ ክንዱን ባያጥፍስ
ምን ሊዳብስ ?
ይበናል
አሻራው ይጠፋል
ውሉ ያለውል ይፈታል
የተካኑዱት ቃልኪዳን ሳይካዩዱት ይወድማል ።
መጬነቱ ማቅረቡ ማቆራኘቱ
ባንድ አዋዶ ማጓተቱ
የልቦናን ድንበር ቀዬ ጠቀስ ማስፋቱ
እያደር ያንሳል ግምቱ
እያደር ይሆናል ከንቱ ።

የሕይወት እልፍ ሺ እጆች
ያበሩልን እልፍ ሺ ችቦዎች
በአጋጣሚ ነፋስ በቅጽበት ሽውታ
እልም ይሉ ጭልም
ክስም ይሉ ድርግም
ደቂቃ ዓመታትን ድል ስትመታ
ገጠመኝ ገጠመኞችን ሲረታ ።

እና ለዚህ ነው ፤
ትንሽ ሽንቁር ትንሽ ስብራት



የመርፌ ቀዳዳ ስፋት ያላት
ከፍቅራችን ብትሠርጽ ብትወጣ
ልቤ ጨጎጊት ያወጣ ፤
አባቶች እንዲሉ
ውሾች በቀደዱት ጅቦች ይገባሉ ።

* * *

---

1965

## ያባትህ ልጅ

እሁን እንዳንተ ማን ሊመጣ
አባቱን መስሎ የወጣ ?
እንዳንተም ያባቱ ልጅ የለ
ጥበብን አቅሮ የገደለ
አወፍሮ ያሰለለ ፥
አንድም አንተን መሳይ—አባቱን መሳይ የለ ።

አባትህ
በግዕዝ አጥር ንቁግ ሕይወቱን ቀጽሮ
ከመላእክት ጋር ታፍሮ
ከሰማዕታት ተተራጉሞ
ከመናፍስት አግቦ ገጥሞ ፥
ያድባር ያህል ተፈርቶ
ካድባር ይልቅ ጉልብቶ
አሸለበ ፤ አንተን አምሳያ ልጁን ተክቶ ።
አባትህ
የቋንቋው ካዝና የምስጢሩ
ስውር ፥ የእንቆቅልሽ ድርድሩ
የመደርደሪቱ ተአምር—እኩይ ግብሩ ።
"በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ"
ሐያሲ—የራዕይ ቅርጽ
በእሳት ልሣን ተናጋሪ
የመለኮት ቃል ፈካሪ ።
አባትህ
ሰደድ እሳት ምላሱ
አይፈታ ጥበብ ቅርሱ
አይገለጥ ምስጢር ውርሱ ፤
ደስስ ይበለው—አንተን አደረሰ እምታደርሰው
    አንተን ወለደ እምትወልደው ።



ከሕይወት] ወዲያ ላያልፍ የጥናትህ መደቡ
ከሕዝብ ጉያ ላይርቅ የምርምርህ ክበቡ
ምን ብትረቅ ምን ብትርቅ እምትደርስበት ግቡ
ወይ የመነሻህ እርካቡ ፤
የስንቱን ዐይነልቦና አታለልክ
እስተዋይነቱን አጭበረበርክ
እንዳባትህ—በቋንቋ ግርዶሽ እየተጠለልክ ።

በጆሮህ ጥጋት ላንሸዋሸወ የአፍርንጅ ልሣነ ነፋስ
አባክንክ ዕውቀት ምርትን—
እንዳይደርስ ከሕዝብ አእምሮ ምላስ ።
የዋህ ፍሬነገር በባዕድ ቋንቋ ተሞሽሮ
በሐሰት ግርማ ሞገስ ታፍሮ
በእኔነት ትዕቢት ተሜፍሮ
ለየህ ፤ ከሕዝብ ደማቅ አደባባይ
ገደመህ ፥ በሉባኤ ከብቸኛ ምልካይ ።
አማያውቁትን ይፈሯል
እሚፈሩትን ያከብሯል
ሲባልማ ሰምተህ ይሆናል ።
አባትህ
ራሱ በማይፈታው እንቆቅልሽ ፥ ተረብ የድግምት ወጀቦ
ፈውስ እያለ ሲያደባይ ፥ የስንቱን ሰው ቀልብ ሰልቦ ፤

  ሰዊራ—እሽዊራ—ሩሽዊራ— አቁራ—ነቂራ
  አዝቢራ—አዥበርቢራ—አጽቢራ—አጽበርቢራ
  ሐሊል ላሒል ቃኢል ባኢል ናኢል
  ባባባላላላፌፌፌዳዳዳ—ሀሀሀ(ሀ—ሀ—ሀ!)

አንተም የመዘለፊያ ልጅ ዛቢያ
ዘመናይ ደብተራ ፀባያ
ተጠበብኩ ስትል ጠበብክ
ዐወቅኩ ስትል ደነቆርክ
መቅረዝ ሲሉህ—እንቅቡም አንተው ሆንክ ።
እና ከአባቴ የተለየሁ ነኝ—
ኢያልክ ብትለፍፍ ብትቃጅ

ሥራህ ይታዘብሃል መሆንህን የሱ ቅዳጅ
የመንፈሱ ንድፍ ወረቀት
የገዘፈበት መስታወት
የደመቀበት መጽሔት ።

እረ ካንት ወዲያ ማን ሊመጣ
አባቱን መስሎ የወጣ
እንዳንተም ያባቱ ልጅ የለ
ጥበብን አቅፎ የገደለ
አወፍሮ ያሰለለ
አንድም አንተን መሳይ—አባቱን መሳይ የለ ።

* * *

.1965



# የንፉግ ምጽዋት

ያን የዘመን ጉዲፈቻችሁን ፤
ያደፈረስ ዐይናችሁን
ያቀጠነ ድምፃችሁን
እባካችሁ ፤ አላምዱኝ ፍርሃታችሁን ።

ያን ቀን ኦቶቡሱ ላይ
ስትሣፈሩ የሆነውን ሳይ
ከአንቀልባው እንደ ሾለከ ጨቅላ
ነብሴ ሙሽሽ ከሾህ ተንጋላ ።
ደማቅ ሰማያዊ ቦጌ ታጥቀህ
ጭስ መሳይ እጀ ጠባብ ለቀህ
ኮት ብለህ ዕድፍ ደርበህ ፤
በግራ እጅህ ከዘራህን
በቀኝህ የልጆችህን እናት ጨብጠህ ፣
ገባ ስትል "ወንድምዬ" የሌላው ዐይንኮ ገላመጠህ!
ኮስታራ ገጹ ገረመመህ ፣
በሹክሹክታው አገለለህ
ባንድ አድሞ አንተን ለየህ ፣
አትጠጋን አትቅረበን አለህ!
ከፊቷ አንገቷ ጠቁሮ ፣ ደረቷ ጠቁሮ
እግሯ በንቃቃት ተቦርቡሮ ፣ ተሸርሽሮ
ቦብሊን ሸንሽና ለብሳ
በላዩ ዶቃ ነገር ፣ ጨሌ አፍሳ
ጸጉሯን በቅቤ አርሳ
ሙጮዋን እንደ ጨበጠች ፣ የት ትቀመጥ ፣ የት ታኖራት?
እንደ ላስቲክ እየሰፉ ቦታውን አጠበቡባት ።
በልብሷ ተጠየፏት ።
በጠረኗ ተሰቀቋት ።
እስቲ በል ፣ ይህችን እናት
የሀገሬ እናት የት ታኖራት ?

ካርኒ ቆራጮ፡ የተግባር ቃሉን ነፍጓችሁ
ቀና ድምፁን ደብቋችሁ
ኋላ ወስዶ ፥ ከዕቃ ጋር ሲወሽቃችሁ ፥
አሳዘነኝ አስለቀሰኝ መራቆታችሁ
ዐልፎ ከእድፋም ልብሳችሁ ።

ግን የኔ እንባ ፥ አልጠፋኝም ኑንደሆን የይስሙላ
የንፋግ ምጽዋት ዘለላ ።
ወይ የቅንጦት ወለላ ።
እናንተ እንጂ ፥ እናንተ እንጂ ወዛችሁን ያነባችሁ
እናንተ እንጂ ፥ እናንተ እንጂ ሰቀቀኑን የቻላችሁ
. . . .ዳፈን ፥ ለታሪክ ዋስትና የከፈላችሁ ።

* * *

---

.1965

ለታሪክ ፈለግ ዉ.ፍ ለሆኑ ወገኖቼ



# እዩ የኔ ዝምታ ጋግርት

እዩ የኔ ዝምታ ጋግርት
አይወለድ ቃል—አጥንት ።
    በከተማው በገጠሩ
    በአምባው በሸለቆው በዱሩ
    በየቀየው በየዕድሩ
    ኡኡታ ሲቀልጥ እሪታ
    ፍጥረት ባነደበት ሲማታ ፤
ሆን ብዬ በጆሮዬ ላይ ተኛቼ
የልቤን ወያኔነት ቀጥቼ
ፍርሃቴን—አብሮ አደጌን ተማጥኜ
እኔው የኔኑ ድምፅ ተሠቅቄ
እኔው የኔኑ ልሣን አፍኜ ፤
    ሲጉነተ ሎኝ ጸጥ እርጭ
    ሲነካኩኝ ጭጭ ምጭጭ ።
እዩ የኔ ዝምታ ጋግርት
አይወለድ ቃል—አጥንት ።

* * *

---

.1965

ግጥሙ ለማይመለከታቸው ፤ በ1965 ኢጅግ እየከፋ የመጣውን ረኃብ ላጋለጡ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ።

## ልጅቱ — የዘመኑቾቱ

ልጅቱ— የዘሙኑችቱ
ጢቱን ብድግ ንሥት
ትለውና
ፊቷን ትጥብ እሽት
ፍትግ ፍትግትግ
ዱሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፋሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈሯን ቅብት ቅልት
ታደርግና ፤
ልጅቱ - የዘመኑችቱ
ሱሪዋን ለምምበጫሙን - ሱርት
ጫማዋን ነጠላውን - ጭምት
ቀበቶዋን ሰፊውን - ቅብትት
ጃኬቷን የቆዳውን - ጅክት
ታደርግና ፤
ልጅቱ - የዘመኑችቱ
መስቷቱ — ትልቁ መስቷት ፊት
ትቆምና ፤
ሣቅ ግጥጥ. . .ሣቅ ግጥጥ . . . ሣቅ
ደርሶ ፍልቅ. . .ፍልቅልቅ. . .ፍልቅልቅልቅ
ከንፈር ገጠም . . .ደሞ ከፈት. . .
ደሞ ገጠም...ገጠምጠምጠም
ወደኋላ ሒድት. . .ሒድት
ደሞ ምልስ . . . ምልስ . . . ምልስልስልስ
ሽንጧን ሰበር. . .ቅልስ. . .ቅልስልስልስ
ዳሌዋንም ውዝ ውዝ
ቂብ ቂብ. . .ቁንን ቁንን
ክው ክው . . .ጅንን ጅንን
ደሞ ፈገግ. . .ደሞ ቅጭም.. . .ቅጭምጭምጭም
ዐይኗን ከፈት. . . ደሞ ጨፈን. . .ስልምልምልም



ደሞ ጉርጥ. . .ደሞ ጥቅስ. . .ደሞ ጉልጉል
(በራሷ ትቀልድ ይመስል)
ልጅቱ - የዘመኑችቱ
ፕሮፋይሉ ብሎ ጥቅልል
ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥተ
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት !
"ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጢት መነሣትሽ ?"
ደሞ ማለት ።
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጺሎታቸውን ዝንግት
"ወይ ጉድ መበላሸት"
አርዝመው እያዩ ማለት ።
ልጅቱ - የዘመኑችቱ
ገሪብ ገሪብ እያለች
እማየዋን እያሣቀለች
አባዬዋን እየገረመመች
ቦርሣዋን እንደ ቦረሠች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሑድ ጢቱን ባንድ ሰዓት ውልቅ ያለች
(አፍታም ሳትቆይ—ወድያውኑ)
ሰኞ ጢቱን ምልስ ትላታለች ።
ልጅቱ-የዘመኑችቱ ።

* * *

---

.1965

# ስንብት

ዋ! አንቺ የምኞት አጥናፌ
የየዕለት ራዕይ ንድፌ
የሕለኝታ ምዕራፌ
    ሁነትሽን ጠላሁት
    ኑሮሽን ተሠቀቁት
የማትጨበጪ ጉም
የሕልም ሕልም ሕልም ።

ሔጄ ሔጄ ፈለግሽን ተከትዬ
ጉልበቴን አባክኜ ቅስሜን ጥዬ
እንደገና ወደኋላ . . .ወደኋላ
ከቁም በድኔ ጥላ
ከዕንባዬ ከለላ ።
እስቲ እዩኝ አስተውዩኝ
ባይኖችሽ ጨረር ሞሽሪኝ
ለጥዑም ዜማሽ አዛንጊኝ
በቃለ ልብሽ አጽናኚኝ፤
ብልሽ ለማታደምጪኝ
በነበልባልሽ አቃጥይኝ!

ግድየለሽም ተይው ይቅር
ላልተጋባን እንዳበል
ላልተኋኋን እንዳለል ።

እስቲ አባክሽ፤ ለሞቴ ልማፀንሽ
የመንፈሴ ቦግ ቦግታ ጠይሞ
የተስፋዬ ተግ ተግታ ተስለምልሞ
አባክሽ፣ ላልኖርኩኝ አታቁሚኝ
አባክሽ ላልሞትኩኝ አታፅተኚኝ ።
ታሪክ አይደል ገድልኮ ነው ለኔ እሚጻፍ
ካንድ የዕድሜ እንኝ እስከ ሌላው ጫፍ
ቀኬትዬሽ ስውተረተር ከጽንፍ እስከአጽናፍ፣



መስሎኝ ፍቅርሽን ብቻ ያመለኩ
ውዳሴሽን ያነበነብኩ
በራሴ ላይ አስማት ደገምኩ
    መተት አዞርኩ ።
በይ ስንት ቀን
ስንት ቀን ባንቺ ሰቀቀን
ባንቺ ላይ ያለኝ እምነት ባንቺ ላይ ያለኝ አለኝታ
እንደ ሰዓት መሙያ ጊዜ እየቆጠረ ይፈታ?

ግዴለሽም ተይው ይቅር
ላልተጋባን እንዳበል
ላልተኋኋን እንዳለል ።

ምነው ዞትር በሩቅ ሣቅሽ መጠውለጌ
ምነው ሁሌም በሩቅ ዳናሽ መበርገጌ
በሩቅ መዓዛሽ መግተርተሬ
በሩቅ ቃናሽ መሰበሬ
ላይለወጥ ዕድሌ ላይለወጥ ዕድልሽ
ላልወጣ ከክበቤ ላትወጪ ከክበብሽ?
ለምን ፋይዳ ወፍ ሁኜ መዘመሬ
    ለጉጀዬ ተጠፍሬ
የዕጣችን ግንባር—ገዶል
    ሳይደለደል ።
ላያመጣሽ ጉርሯ
ላያጉዘኝ ዶፉ
አፋፉ ላይ ቆሜ
ላይቃና ስቡሬ ቅስሜ፣
ላላርፍ ከዕድሜ ልካ ሕመሜ
ላይሻለኝ የጣር ዘላለሜ ።
አባክሽ ተይኝ
የዋህ አማኝ ብልሽ ማሪኝ
ጅል አፍቃሪ ብለሽ ናቂኝ ።
ጽድቅሽን ብዬ ኩነኔ
ፍቅርሽን ብዬ ምናኔ ።
ድንገት የወረዶ አሎሎ

እንደ መብረቅ ክንድ ተገንጥሎ
እንዳይከሰስ አቁስሎ
ተበቀልሽኝ፣ ስም ሳይኖረው ለበቀሉ
ገደልሽኝ ፤ ወንጀይ ሳይኖረው ለበደሉ ።

ግዴለሽም ተይው ይቅር
ላልተጋባን እንዳበል
ላልተኳኳን እንዳለል ።
ብቂኝ፣ በሕሊናዬ አድማስ አትታይ
ልገላገል፣ ከትዝታሽ ከጭብጥሽ ሥቃይ
ከመልለምለሜ ብካይ ።

ደኅና ሁኚ. . .ደኅና ሁኝ በይ
ኮከቢቱ የሰማይ እንጉዳይ
የፕሉቶ ላይ ሲሳይ
ጉድባይ ።

* *

.1965



# ፀሐይን ሳያይ ተፈጥሞ

ሲንደረደር ሲንደረደር
ወደቀና ካንቺ ድንበር
ካንቺ እምባ ካንቺ መንደር ፤
አይነማ በምን ፀቅም፣ በምን ሰበብ
የወግ ገደብ ?
ቢችግረው በሩን ዘግቶ፣ እግሮችሽ ላይ ተደፍቶ
ሲልሽ 'ሁኚኝ—ያንቺ አድርጊኝ'፣ መላ መንፈሱን አካቶ
ከዘመድ ዐይን ተገልሎ፣ ካለፈ ሕይወቱ ተፋቶ
በ'እግዜር ቢል ነው' እንደበቱ፣ ቅሬታውን አዘናግቶ
ባንቺ ቆሌ ውሎ አደረ ፤ ባልፎ ሒያጅ ፍቅርሽ ረግቶ ።
ምንም ዐልፎ ሒያጅ ፍቅርሽ ቢሆንበት፣ የሰንበሌጥ የሣር ባላ
ምንም ፈገግታሽ ቢጨልምበት፣ ምንም እያደር ውልሽ ቢላላ
አዚምሽ እንደሁ ወድቆበታል፣ አያልፋትም ያንቺን ኬላ ።
ወረቀት ላይ ያልነጠበ፣ ቃል አለበት አንዳች መሐላ ።
እና ነበልባሉ የከሰመ፣ ዐመድ ብናኙ የቀረ
ገለባው ብቻ የኖረ ፣ አሠሩ ብቻ የተከመረ
ሰብዕናው የጮረረ፣ የነበር ግቱ የነጠፈ
መሆኑ ቅር እያሰኘሽ ከጭብጥሽ እስካላለፈ ።
እሱም ዳግም አይነቃ፣ ይቅር ብይኝም አይልሽ
የከፋት ጽድቁን ነው የሚሻ፣ አይወገሽ በመገደርደርሽ
አይበረግግ በወረትሽ ።
በሲኦልሽ ሲኦል አካብቶ፣ ጭለማሽን አጨልሞ
አለኝታውን አካቶ ፣ በተስፋ መቁረጥ ከርችሞ
አኖሻሽ ተቀብሮልሻል፣ ፀሐይን ሳያይ ተፈጥሞ
ፀሐይን ሳያይ ተፈጥሞ ።

.1965

# ሽር በይበት ሽር

ሽር በይበት ሽር
ሽር በይበት ሽር ቢያሙራው ጉዳና
በየኮሪደሩ በየቢሮው ካዝና
በየስርንጉጡ— በየስርጣስርጡ
        በየጉጣጉጡ በግጡ በድጡ ፤
ሽር በይበት ሽር
ሽር በይበት ሽሮ ከንዳ— አደባባይ
        ከታሕት እስከላይ
በዝንተ ዓለም ፍና በለሆሣሥ ዳና
በባህል ዳዋ ውስጥ በፍጡር ገበና ፤
ሽር በይበት ሽር !
ያንቺን እግሮች እሚያስር ሰንሰልት ካቴና
የቀጠቀጠ ጣት የፈጠረ ሕሊና
ቢሹት ቢሹት ቢሹት
        ይኸው እስከ ዛሬ አልተገኘምና ።

* * *

.1966



# ዘመዴን ስስመው

ዘመዴን ስስመው
ጉንጬ ቢሻክረው
እኔንም ሻክረኝ ፤
ዕድሜ መለስለሱ ማብቃቱ ታወቀኝ ።

* * *

.1966

# አንተን በመኻል አያሳጣኝ

አንተ ነህ ጓደኛዬ
የምስጢር ጌጥ ሙዳዬ
(የብል ማከማቻዬ)
አንተ ነህ ጓደኛዬ ።
ሌላም ጓደኛ አያሻኝ
አንተን በመኻል አያሳጣኝ ።
አንተ ንቁ ብርቱ ማግኔት
እኔ ሌሎች የግራ ቀኝህ ብረት ።
ባንተ ፀልፈው ነው እሚያዩኝ
ባንተ ዘልቀው ነው እሚሰሙኝ
አቦ አንተን አያሳጣኝ
ሌላ ጓደኛም አያሻኝ ።

አንተ ሠናይ፣ የዜማ መምህር
ዘፈኔን እምታንጐራጉር
አንተ ብርቱ ባለቅኔ
ዘራፌ የስንኝ ውጥኔ ።
አንተ የኔ ስማበሎ፣ አንተ አፈእኔ
ቁንጣኔን የምታስታግሥልኝ ጠኔ
መለኪያዬ—የዐረብ ቤት ሚዛኔ
ካጠገቤ እማትለይ የመከራ ቀኔ ።
ሌላ ጓደኛም አያሻኝ
አንተን በመኻል አያሳጣኝ ።

ወደኔ የሚፈሱትን ወንዞች ከትርልኝ
ኩሬ እንጂ፣ ባህርኮ አይደል በልልኝ
በደግነቴ እንዳልጐዳ፣ እዚያው ባሉበት አቆይልኝ ።
ታጠርልኝ፣ እሾህ ሁንልኝ አሜከላ
ገድመኝ፣ በአሉባልታ በድለላ
ቀጽረኝ፣ በጠብ ለሐሜት ኬላ
ለኔ ስትል ክፉ ሁንልኝ



ደግነቴን እታውራብኝ ።
ሌላ ጓደኛም አያሻኝ
አንተን በመኻል አያሳጣኝ ።

* * *

.1966

## አለ ፥ 'ጠና በል' እሚለኝ

የብቸኝነት ጥምጡሳሱ
የፍርሀት ግሳንግሱ
በበረዶ እጁ ሲዳስሰኝ
በእሾህ ጣቶቹ ሲቧጥጠኝ ፤
ምላስ ከንፈሬን ሰብስቤ
ዐይኔ ሕሊናየን አድቤ
ከመታመቄ ከወላፈኔ
ከማቄ ከሰመመኔ ፤
ሰንበሬን አመሳስዬ ከኮከቤ ፤
የብቸኝነት ጥምቡሳሱ
የፍርሀት ግሳንግሱ
እንዳልተገራ ፈረስ ሲያደባየኝ
እንደ ደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ
እንደ ተጋለጠ ሐሜት ሲሰብረኝ ፤
አለ ፤ በርታ ጠና በል የሚለኝ ።
በዐይኔ እንባውን አፍሶ
በምላሱ ምሬቱን ላልሶ
ማቄን በካባው አለሳልሶ ፤
ከዋሸንት ፉጨት ጨርፎ
ከቅኔ ስንኝ ጠልፎ
የፉጨቱም ከስንኙም ጨምቆ
ክውብት እዝን ሰንቆ
ቀስተ ደመና አርቅቆ
በርታ ፥ ጠና በል እሚለኝ
አለ ፤ እሚያስተዛዝነኝ ።
የብቸኝነት ጥምቡሳሱ
የፍርሃት ግሳንግሱ
በበረዶ እጁ ሲዳስሰኝ
እንደ ደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ ።

---

.1966



## እሱ ነው — እሱ

እሱ ነው-እሱ
ፀይን ባይኖረው
ለምን ብርሃን ኖረ እሚለው ፤
እግር ባይኖረው
ለምን መንገድ ኖረ እሚለው ፤
እሱ ነው—እሱ
ከቀናቴ
ፀሐይቱን የሰረቀ ።
በመንገዶ
እሚከላ ያጸደቀ ።

* * *

---

1966

# ድኅረ አብዮት ግጥሞች

# ዛሬን እንኳን

እስቲ ዛሬን
    ዛሬን እንኳን
    ዛሬን እንኳን ግቂ፤
እስቲ ዛሬን
    ዛሬን እንኳን
    ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ፤
    አትደብቂ—ፈገግታሽን አትፋቂ ።
ኮረቤት አይታዘብሽ
የሐሴት ደመኛ አያርግሽ
እባክሽ፣ እናት ዓለም እባክሽ ።
የዕጣሽን አድማስ ጉም ሸፍኖት
ምድር-ሰማይሽን አጨልሞት
ፀሐይሽን ቢጠልብሽ
ጨረቃሽን ቢሠርቅብሽ
አንቺ እማዬ እንደ ሌሎች፣ መሣቅን እማታውቂ ነሽ?
በዕንቁጣጣሽሽ ዋዜማ ድንኳን
በተቀጣጠለው ችቦ ውጋጋን
ፈካ ይበል የገጽሽ ብርሃን
ደመቅ ይበል የልብሽ ዙፋን
ዛሬን እንኳን፣
    እማምዬ
        ዛሬን እንኳን ።
ለኛም ችቦ አዳርሰሽን፣ ኢዮሃ አበባዬ እንበል
በውሃ አይደል፣ ዛሬስ በቃል በሁካታ እንጠበል ።
ተቸንክሮ እንደኖረ በር፣ በትግላችን ተለማምጠን
እንደበቃችንን ተማጽነን፣ ከንፈራችንን አላቀን
ቢኮለድፍ ምላሳችን፣ ባይጥም እንኳን ዜማችን
ቢሰባበር ድምፃችን፣ ዝርው ቢሆን ነገራችን
ብቻ እንጩህ ፍቀጅልን— ጩኸት ነው እኛን ያማረን ።
አወን ጩኸት ነው እኛን ያማረን፣ በጩኸት እንንበልበል

የገደል ማሚቶ ትንታ ፥ ከእንቅልፍ ትራሷ ትከንበል
ከቦዘን ሕልሟ ትፈንገል ።
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ ፥ አዕምሯችንን በክሎ
ቃል አስጥሎ ሐሳብ ገድሎ
ያይንን እውነት በአርምሞ አሰልስሎ
የጆሮን ታሪክ በዝምታ አብጠልጥሎ
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ ፥ አእምሯችንን በክሎ ።
የጣር የጭንቅ ድምፃችን ፥ እንደ አምና ዛሬ ይድረስሽ
የዘመናት ቅርሳችን ፥ ወጥቶ ፊትሽ ይቅረብልሽ
የፍሬያችን የምሥራች ከቶ ምን ቢሆን አንነፍግሽ ።
ከኛ ፈገግታ አትጠይቂ
ከኛ ሐሴት አትጠብቂ
እንባም ለኛ ተስፋ ነው ፥ እባክሽ ስለ እንባችን አንቺ ማቂ
አንቺ ፥ ስለ ጩኸታችን ፈንድቂ
አንቺ ፥ ስለ ጭንቅ ድምፃችን ቦርቂ ።
አለመሣቅኮ ይቻላል ፥ አለማልቀስ ነው ጭንቁ
የመንፈስን እንጉርጉሮ ፥ በመንፈስ እምባ ማመቁ
ውስጥ ውስጡን እየደሙ ፥ በቀቢፀ ተስፋ መድቀቁ
ለተሰለመለመች እውነት ፥ የደም ደብዳቤ ማርቀቁ
በቅሬታ ሰደድ እሳት ፥ ሕዋሳትን መጨፍለቁ ፤
አለመሣቅኮ ይቻላል ፥ አለማልቀስ ነው ጭንቁ ።
እና ፤ እስቲ ዛሬን
ዛሬን እንኳን
ዛሬን እንኳን ማቂ ፤
እስቲ ዛሬን
ዛሬን እንኳን
ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ ፤
አትደብቂ—ፈገግታሽን አታርቂ ።

ሚያዝያ — 1966



## ብቻ መገኘትሽ

እንደ ናፋቂ ሕፃን እናቱን እንዳየ
በደስታ ሐዘን እንደ ተሠቃየ ፥
እንባውን እንዲያዘንብ ለሐሴቱ መቅድም
ዐይንሽን ባየሁኝ እንባዬን ባፈስም ፤
ወይም
ታውሮ እንደ ኖረ እንደ አንድ ጐበዝ
በድንገት ብልጭታ እንዲደነዝዝ
በጨለማ ቤቴ አንቺ ጮራይቱ
ዘው በማለትሽ ቢጠፉኝ ብልሃቱ ፤
እንባውም ይደርቃል
ብልሃቱም ይገኛል ፤
የወጣሽው ፀሐይ ጽልመቱ ሲሸሽ
ብቻ ሙገኘትሽ
ብቻ መኖርሽ ።

* * *

ሚያዝያ — 1966

# ሐዘንሽ አመመኝ

ውል አልነበረንም የፍቅር ቀጠሮ
ቃልም አላኖርንም በወግ ተቀምሮ ፤
እኔ አንቺን እንዳላይ
አንቺ እኔን እንዳታይ አምባችን ተቃጽሮ
ዕጣችን ተካሮ ፤
ቀለምሽ ከዐይኔ አሻራሽ ከጣቴ ባይጠፋ ተማትሮ
(አትብት እምብርቴ ሁኖ ንንዲኖር ደድሮ)
ይኸው አካየደን በደንገት ዘንድሮ ።

የገጽሽ ብርሃን ቢጠይም ፀዳሉ
ድምፅሽ ቢቀጥንብኝ ቢሠልብኝ ቃሉ
ወዘናሽ ቢማስን ዛሬ ያለውሉ
ፀአጆችሽ ጨበጡኝ ሐዘንሽ ሥዕሉ ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

ጀንበር ነሽ አበባ ሕይወት ተስፋ ዘቦ
ፋሲካ ዕንቁጣጣሽ ማኅሌተ ገንቦ
ብዬ ያወደስኩብት ታዘበኝ ዘመኔ የትላንታት ቀኔ
ዛሬ ሲጮህብኝ ቅኔ እንዳይደል እውኔ ፤

ሐዘንሽ አመመኝ ።
ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

የገደል ማሚቶን ታዘብኳት ተኝታ
በጩኸትሽ ማዕል አኩርፋና ታክታ
ላንቃዋ ይታየኛል ደም ለብሶ ደም ጐርሶ
ቃልሽ ያለፈበት በጭንቅ ተለውሶ ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

ጽጌያቱ ደረቁ ንቦችሽ አለቁ ሰዎችሽ ደቀቁ
ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ ፤



ዐዋይን ሰማኋት ዕታለቅስ በይፋ
ከጐጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፋ ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

አላውቅልሽ ብዬ አታውቂልኝ ብዬ
እምነትሽን ጥዬ ፍቅርሽን ገድዬ
አኩርፌሽ ስቀመጥ ያው እንደ ባላንጣ
ይኸው ነጭ ማተብሽ ሊያስታርቀን መጣ ፤
ሐዘን ነው ውበትሽ ውበት ነው ፍቅርሽ
ብርሃን-ጥለት አልቦ ጌል ነጠላሽ
ፀይኔን የገለጠው ጥቁር ጨለማሽ ፤...

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

* * *

ግንቦት — 1966

# ለድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች

ታዲያ ዛሬ ፥ በሰበብ ባስባብ ሰንሰለት
ተጋምደህ ብትግጊት
ብትቋሰል ብትዛበት
ብትናፈር እንደ ርጥብ እንጨት
ብትዳቆስ እንደ መርግ ንዶት ፤
ታዲያ ዛሬ ፥ ባደባህበት አደባባይ
በነገር በተረብ ሥራይ
በደባ በሾርኒ ግዳይ
ልግነን ስትል — ብትፋረስ ብትጣጣል ብትሻወድ
ልድመቅ ስትል — ብትንኳሰስ ብትማገል ብትፏደድ ፤
ታዲያ ዛሬ ፥ የወግ ጽዋ ብትጣጣ
ብትፋታ ብትዳበል ጦጣ ለጦጣ
በቋንቋ ብትናገድ ፥ ብትጧደን በአፍ ዶፈጣ
እንደ ርችት ብትንጣጣ ፥ እንደ ፍግ የትም ብትሰጣ ፤
ታዲያ ዛሬ ፥ አስተናግር እንደ በላ
ሺ ምላስህን ብታቁላላ እልፍ ትናጋህን ብታላላ
ሻካራው ልብ—አንደበትህ ፥ በአራራይ ዜማ ቢሰላ
ለማኙን ቀርቶ ጥላውን ፥ ለማቀፍ እጅህ ቢያደላ ፤
ካልሆነ ፥ የታሪክን ሐቅ አምኖ ፥ ይቅርታውን ለመማጠን
ካልሆነ አትራህ ጠናኝ ብሎ በአዲስ ፍኖት ለመፋጠን
ማነህ በእቻምና ፥ በአቻምና በስቲያ
አዳፍነህ የእምነትን ቋያ
ኑብስህን ከተህ በወኔህ ጉያ
ለዐይንህ ዐይን ፥ ለአእምሮህ አዕምሮ ፥ የሰጠህን ባለአም
ረስተኸው ርቀኸው ድንጋይ አልብሰኸው በበረሃ ፤ . ..
የፍርድን ጨኸት አቤቱታ
የማወቅን ሕመም ቅሬታ ፥
ሕሊናህን በማባበል
በየምናምኑ በመደለል
ያላዘናጋህ ያልተዘናጋህ
ማነህ? እስቲ ማነህ'



ከማይመስሉህ ተቧድነህ ፥ ባንድ ሠምረህ
ኩኩሉ አልነጋም ፥ አይነጋምም ብለህ
ለፊውዳል ቅኝት ነዝረህ ፥ ለቡርዧ ከበሮ ተደልቀህ
ለኔነት በኔነት ማራቶን ተጣልፈህ
ለክብር ለንዋይ ተዳፍተህ
ለስም ለዝና ተዳምተህ
ነቀዝ እንደ በላው እህል ቀለህ
ዋግ እንደ መታው መኸር ሻሽረህ
መልሕቋ እንደ ጠፋ መርከብ ሰፈህ
የትም ነፍስህ. . . .የትም ባክነህ. . .የትም ደቀህ ፤
የኔሮንን ሣቅ ያልሣቅህ
. . . .ማነህ ፥ እስቲ ማነህ ?
ካለህ ፥ እኔ ነኝ በል. . .በል
ላንተ ይገባሃል ፣ የሰማዕት አክሊል ።

* * *

ግንቦት — 1966

## ጿጥኙ

መሠረቱ ጽኑ
የብረት ምሰሶ ነኝ ባይ
ቋጥኝ በጿጥኙ ላይ ፤
ንፉስ ራሱን ያዞረው
ሣር ቅጠል ድንጋይ ዐፈር
ቁብርዓራ ነገር
ሲኮረኩመው እንዳከከው
ሲገፈትረው እንደ ዳሰሰው ፤
(ትዕዝብቱ ብቻ እያሣቀው)
ግና አንዴት ጠቢቃ. . .አንዴት ጠብታ
ውሃ ተሰኝታ
አፈር ስትነክስ
ድንጋይ ስትጎርስ
ውቅያኖስ
(መርከብ እምታፈርስ)
እና መች ቀረለት መነጠቁ
ከግሸር ዳሱ መውልቁ
እንዲያ እንዳልተ ነከተቱተ—
እንዳልማቀ ፤
ወደ ቁልቁል
ወረደ
ቋጥኙ
እየ
ተን
ሰተ
ሰ
ቀ

.መስከረም 1967



## በትን ያሻራህን ዘር

በንጥ በስርንጉጡ
በማጥ በድጡ
እንደ ተንጋለልክ—እንደ ዘመምክ
ትንፋሽህን እንደ ቋጠርክ
ልል ቀበቶህን እንዳጠበክ ፤
የተልእኮህን አባዜ
የሕይወትህን ቃለ—ኑዛዜ
ወርውር !
የእጅህን ዘገር ።
በትን !
ያሻራህን ዘር ።
ይዘኸው እንዳትቀበር ።

* * *

.1967
የምቾት ሱስ ለሌለባቸው ለሀገሬ ልማትና ዕድገት የትምና መቼም ቀና ደፋ ለሚሉ ።

# ትዝታን ማለስለሻ

አየሽ ፥ አንድ ቀን ደሞ. . .ደሞ
የሔዱበት መንገድ አዝግሞ
ይመጣልና ከርሞ. . .ከርሞ
ሲጋፈጥሽ. . .ተግ ሲልብሽ
ጭለማዬ ሲበርቅብሽ
ጭንቄ ገዝፎ ሲጋርድሽ
አትበርግጊ አይጸጽትሽ
ዝምታዬ ሲጮህብሽ ።

ለቅሶ ትካዜ መብከንከን
ፍቅር ጥላቻ ሰቀቀን
ቅናት ቅሬታ መማስን
ጨረር ላይኖር ፥ በቀቢፀ ተስፋ ደን ።

ተፈጥሮ ፍሬን አልቦ
በማጥ በስርጓጉጥ ተስቦ
አበቃለት ነዶ ከልቦ
በድንፋታው ተገማጥቦ ።

እና ለመውደቅ ለመንከባለል
ተፈጥሮን እሚያህል ገደል
የት አል
ብዬ ነው ፤
እኔው
የተበዳይ ይቅር ባዩ ራሴው
እንባዬን ከዐይኖችሽ እማብሰው ።

.1968



# ገና በልጅነት

ገና በልጅነት. . . .
ገና በእጅነት እርጅናውን ኖሮ
ገና በአፍላነት . . . .
ገና በአፍላነት ከዕድሜው ዳር ተሻግሮ ፥
ጀንበሯን ሲያስተውል
ቀለሟን ቻል ብሎ
ሙቀቷን አፍቅሮ ፥
ጨረቃን ሲታዘብ
ድምብል—ቦቃን ትቶ
አበባዋን ጥሎ
ብርሃኗን አንሥቶ ፥
ገና በልጅነት. . .
ገና በአፍላነት. . .
ከብርሃን ከሙቀት ምስሉን ለመከወን
ሐውልቱን ለማቆም
ሲወድቅ ሲነሣ ሲለፋ ሲታገል
ሲጣጣር ሲዳከም ፤
ብርሃንና ሙቀት ሐውልት አልሆን አለ
ቀለምና አበባ ሳይከሰቱ ኃብረው
ኃብረው ሳይሳሉ ።

* * *

.1968

# መንታ ነው ፍጥረትሽ

ተገልጠ ዕቶኑ ተከፈቱ ዐይኖችሽ
  ብርሃን አዘነቡ ፤
ቀለማት አቅርረው ውበትን አነቡ ፥
ጋረዱት ኮከቤን ብርሃን አጠሉበት
ኩራዜን በማሾ አዳናገዙበት ።
ከንዶችሽ አቀፉኝ አቅፈው አባበሉኝ
  አባብለው አስተኙኝ
ውጋቴን ነጥቀውኝ ቁስሌን አዘናጉኝ
ከሰመመን ጀርባ እሸህ ላይ ሊያነቁኝ
ቁርንጮ ሊያለብሱኝ ፀማቅ ሊፈትጉኝ ።
ሰጠኸኝ ጨለማዊት ወለፈንዴን ጽዋ
ባንድ የተቀመመን ማርና ግራዋ ።
ምን ይሆን ፍጥረትሽ ጥንድ የሆነ መንታ
ከቃልሽ ያልጠፋ ብሥራትና መርዶ
        ዋይታና እልልታ ።
ያልታሸች ሙሽ ነሽ የዕድመኞች ጨዋታ
የሐሴት ርኅት የሐዘን እሩምታ ።

* * *

.1968



# ፀቀበሮ ጉድጓድ

ፀቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው
ፀቀበሮ ጉድጓድ ቀፀሮ መስሏቸው
ውሾቹ አጓሩ ፀዛ ጩኸታቸው
አየሩን በከለው
ምድሩን አገረኘው — ትፋት ድንፋታቸው !

አይ የውሾች ነገር ፥
  ማን በነገራቸው
  ማን ባስተማራቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው !
አንፀሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው !

* * *

1970 ለአብዮታዊት ሀገር ወጣት ጀግኖች

## ጥሬ ጨው

መስለውኝ ነበረ ፥
የበቁ የነቁ
ያወቁ የረቀቁ
የሰው ፍጡሮች ፥
ለካ እነሱ ናቸው ፥
ጥሬ ጨው. . .ጥሬ ጨው
ጥሬ ጨዋዎች ፥
መፈጨት — መሰለቅ — መደለዝ — መወቀጥ —
መታሸት — መቀየጥ
ገና እሚቀራቸው ፤
'እኔ የለሁበትም !'
ዘወትር ቋንቋቸው ።

* * *

---

.1971
በገለልተኛ ጨዎች ምሁራን ላይ



## አድማሳዊ ፍቅር

ዛሬ ታመመልሽ በትላንት ተለክፎ
አድማሳዊ ፍቅር በእውነታው ጉልድፎ
ድሮውንስ ቢሆን—
ሰማይና ምድር መቼ ተገናኝተው
መቼ ተሳሳሙ ?
ያው እንደኔ እንዳንቺ መስሎት እንጂ ዓለሙ
በምናብ አተያይ በገመት በሕልሙ ።
ልብ በይ
አንቺ ሆይ ፥—
የኔና ያንቺው ጠብ አይደለም የርስ በርስ
ይልቅስ እንጂ ነው የራስ ሥጋና ነብስ
ስሜት እሚመትር ደም እሚያበስብስ
ከራስ እሚያናክስ ።
በዐይኔ ጥዶ ታስረን
በተራ እሴት ታጥረን
በ"ምን ይሉን" ደክመን ፤
ከዚህ የሕይወት ዝፍት
ማኀበራዊ ውርዶ
ምድራዊ አመሳሶ መላቀቁን አጥተን ፤
የነብስን ዋይታ
የጭቅርን ኡኡታ
የሐቅን እሪታ መመለስ ኳቃተን ፤
ለኔዎች ላንቺዎች
ለፍርሃት ልጆች ፥
ለፍቅር ጭንጋፎች
ለፀፀት አምራቾች ፤
ከዋክብት ይውደቁ
አፀቦች ይድፈቁ ።

---

.1972

## መስከረም

(በድምር — የሴትና የወንድ—ኅብር ድምፅ)

በሰማያዊ መስከረም ሰማይ
የፈነጠቅሽ አብዮት ፣ ፀሐይ
ብሩህ - ዕንቁጣጣሽ - ሲሳይ ፤
ምን ያህል ዘመን ምዕት ዓመት
ምን ይባል ትግል ምን ጥረት ፤
አድኅሮትን ያህል ጨለማ
ጨለማን ያህል ጠላት
ፈግጦ በድል ለመምጣት ? !

(በነጠላ — የሴት ድምፅ)

በሉ ፣ ማን ያርቅ ቅኔውን
በሉ ፣ ማን ያትት ታሪኩን
   የጨለማውን ?

(በድምር— የወንድ ድምፅ)

ያንቦካቦከው ወይ ቅጠሉ ፣ ያዥጎድጎደው ወይ አምባው
ያንጉራጉሩት ወይ ወንዞቹ ፣ ያጉረምርመው ወይ ተራራው
ዋ ይበልለት አሞራው ፣ ያስካካለት ወይ ጥንብ አንሣው
ያስገምግምልት ወቾገል ፣ ያላዝንለት ወይ እንስሳው
ፀዋይ ታቃስተው ይሆን ፣ የገደል ማሚቶ ታልቅሰው
ወይስ አድባር ትጮኸው. . .

(በድምር — የሴት ድምፅ)

አይሰብረውም ወይ
የያሬድ ዜማን የቀከሌን ቅኔ
ይካተታል ወይ
በዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍናና የዱሬ ምናኔ
አይዘለውም ወይ



ገድል ስንክሳሩን ተአምር ድርሳኑን
የዓምደጺዮንን ዜና መዋዕሉን
የሳባን ተረት ክብረነገሥቱን
የካህኑ ዮሐንስ ዐይናማ ቃሬር ያን መስተዋቱን
ልፋፈ ጽድቁን ዐውዶ ነገሥቱን
የአባ መጣፉን የሼህ ኪታቡን
   አይዘለውም ወይ

(በነጠላ — የወንድ ድምፅ)

ታድያን ማን ያርቅ ቅኔውን
ታድያን ማን ያትት ታሪኩን
   የጨለማውን ?

(በነጠላ — የሴት ድምፅ)

አብዮት — ጽን
ዝማሙን የፈታላችሁ ልጓሙን ያነሣላችሁ
ቃል — እንደበት የሰጣችሁ
ብዙኃኑ ተናገሩ ታሪኩ ነው የራሳችሁ
   ቅኔውም ነበር ሕይወታችሁ
   (የሕልም እሳት በየፀረዶ ጐጆአችሁ)

(በድምር — የሴትና የወንድ ኅብር ድምፅ)

የጨለማውማ ታሪክ ፣ የጨለማውማ ቅኔ
ይፋጃል ከክብረ ሰማይ ፣ ይጮሃል ከቦምብ ካዳፍኔ
ያተባል የጭቁን ሐኔ !
ያፍማል የታጋይ ወኔ !

(በጣምራ — የወንድና የሴት ድምፅ)

ጉበዝ ፤—
ከስሜን ተራሮች አናት አቆልቁለህ አስተውለው
በትዝታ ዐይኖችህ ቃኘው ዙሪያ ገባውን ድፈረው
በሸለቆው በአምባው በደኑ ሆነ በፋልማው
በባድማው በበረሃው በቆላው ሆነ በደጋው

እንደ ጥልማሞት ሲንከላወት
ፊትህን እሚጋርደው በተራቆተ ዕብእና
ፀረከሱ እጆች ተጋልጠ
ዐይንህን እሚጋርጠው የህልውናው ገበና
አንደበቱ እንደ በሬው
ተሸብቦ እምታየው በዝማም ጽኑ ካቴና
ይኸ ጉልቄ መሣፍርት የሌለው ይኸ ሁላ የቀትር ጥላ
የትላንት እኔነቴ
የወዲያ ቀን ማንነቴ እንጂ እንዳይመስልህ ከቶ ሌላ
ተረት አፈ—ታሪክ ቅጸላ
መንጠልጠያ የአንቃ ባላ
አንዳች ላንቁሶ ከለላ ።
ሕሲናህ ይፍረደኝ ዘመዴ ፥ ልቦናህ ይይልኝ ወገኔ
ያ እንደነበር የትላንት መልኬ ፥ እሱ እንደሁ የነበር እኔ ።
ጠኔ የጣላት የወፍ ጫጩት ፥ ጭው ጽው ድምፅዋ ነበር ድምፄ
የዘመን እንጕርጉሮዋን የወረሰች ፥ የቆኜም ቃሏ ነበር ቃሌ
የምዕተ ዓመታት ነጭ ማተቤ ፥ የየዕለት ውሎ መስቀሌ ።
ሆዴ ነበር ፤
ስእውድማ ያልበቃው ክምር ፥ የሻሸረው አዝመራ
ጕኔ ነበር ፤
ቦና የበላው ሰብል ፥ የቆመው ቀጥና ከጭራ
ፀይኔ ነበር ፤
የባድማ ዐለት የዐለት ጕተራ
ልቤ ነበር ፤
የዠማ ንፍገት የውሃ አንጡራ
ተፈጥሮና ሰው
ሰውና አድኅሮት ባንድ የፈተሉት ወፈናጅራ
የበጋ ጕርፉ የክረምት ብራ ።

(ፀድምር — የሴትና የወንድ ኅብሮ ድምፅ)

የጨለማውማ ታሪክ የጨለማውማ ቅኔ
ይፋጃል ከክብረ ሰማይ ፥ ይጮሃል ከቦምብ ካፋፏ



ያተባል የጭቁን ሐኔ !
ያፍግል የታጋይ ወኔ !

(በድርቡ — የሴትና የወንድና ድምፅ)

የእግዜር ቤተሰቦች ፥
ጉልተኛ ዕጨጌዎች መኳንንት መሣፍንት ነገሥት ነገሥታት
ልዑል እምልዑላን ካቡር እምክቡራት ፥ ቅዱስ እምቅዱሳት
ብፁዕ ወብፁዓት ጸሐፌ ትዕዛዛት ፥
(የጨለማ ልጆች)
ታግልህና ድምተህ
ያለመለምከውን የታሪክ ባንዲራ የነጻነት ዓርማ
የወዝህን ሰንደቅ የክንድህን ግርማ
ተጠየቅ ታውቃለህ !
ነጥቀው እንዳደኸዩህ በፊውዳል ዘመናት
በዚያ ፀጨለማ !

(በድምር — የብዙኃኑ ድምፅ)

አለ እንጂ የከፋ ከዚህም የባሰ
ታሪክ ሲቋረሱ ገድል ሲዛረፉ ተርፎ ከራሳቸው
ከሰማዕታት ሳይቀር ከመላዕክት እንኳን አሉ የደረሳቸው ፤
ፀዐድዋ ጦር ሜዳ ፀዚያ ቀውጢ ሰዓት ሕዝበ ዓለም ሲዋቃ
አይደለምዪ ጊዮርጊስ ፥ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለታሪክ የበቃ !
የሮሀ መቅደሶች
ዝነኛ ሕንፃዎች ከዐለት ማኅፀን ተፈልፍለው የወጡ
ነው አሉ በመላዕክት ከአርያም ወርደው በሌሊት በመጡ !!
ወንኔ አስተውለው ፥
እኛን የኩሽ ሕዝቦች የሴምም ወገኖች
የጠይሟን አፈር ጠያይም ትውልዶች
ቾሬ — አይመለሌ ፥ መንዜ — አንኮበሬ ፥ ዶርዜ — ወላይታ
ሐማሴን — አጋሜ ፥ ቦረና — ወለጌ ፥ ሐድያ — ከንባታ
አገዌ — ቢለኔ ፥ መጀርቲ — ኡጋዴ ፥ ሣሆ — አማውርታ ፥
እስላም ክርስቲያን ፥ አረሚ ፈላሻ
'ጥንበ — በል ተልካሻ' ፥

ብለው በመደንበር በቀጫጭን መስመር
በቋንቋ — በሃይማኖት — በወንዝ — በመንደር
የአንድነት ግንባችን በማፈራረስ በመሰነጣጠቅ
ለስንት ዘመናት
የጨለማ ልጆች በፍራሻችን ላይ ካቡበት ሠቀሠቅ ? !

(በድርብ — የወንድና የሴት ድምፅ)

ያገሬ አርሶ አደር ያገሬ ወታደር ያገሬ ወዛደር
የሰፊው ሕዝብ ሰፍር የብዙኃን ድምር
ለደቂቃ ቁራጭ ለቁራጪ ቅጽበት ለቅጽበቷ ክፋይ
ከቶ ፀሐይ ሳታይ ፤
በዚያ በጨለማ ታጥረህ ስትሠቃይ ፤
ይታወስህ ወገኔ
የጉልተኛ ልማን የከበርቴ አንደፀት በልፍኝ ባደባባይ
ያወራ እንደ ነበር ሀገርህ እንደ ሆነች የዐሥራ ሦስት ወር ፀሐይ።

(በድምር—የብዙኃን ድምፅ)

በወዜ በደሜ
ሀገሬን ነኝ እኔ ፡ እኔን ናት ሀገሬ
ጦርነት — ሰላሜ ፡ ጤንነት — ሕመሜ ፡ ደስታ — ችግሬ
ደሳሳ ጐጆዬ የቀሳ ትዳሬ ።
ላፍ አይገድምና ባላባት ከበርቴ
እልፍኙን ከሆነ ብፋህ አደባባዩን ሀገሬ ማለቱ
እንደ ዶግ ተማግደን
እንደ ጧፍ ተቃጥለን
ስጥተነዋልና የሐሴት አምቃ የላቀ ጉልበቱ
አሳበለም ከቶ ፡ አምኗል ባንደበቱ ።
አለበለዚያ ግን ባሰት ተጠቅሳለች ሀገሬ ምድሬቱ
ያው እንደ ባህሉ
የባላባት ተረት የከበርቴ ወጉ ተጋኗል ኩሸቱ ።
ማልዶ ከወናፉ ማልዶ ከመጫኛ ማልዶ ከሞተሩ
ማልዶ ከዋግንቦው ሚልዶ ከምድጃው ማልዶ ከቀንበሩ
ሀገሬ — እኔነት ጨልማ ትዳፉ ፡ ጨለማ አጥፉ ።



የጐጆው ጉልላት
የየሸክላ ክፋይ ላንድ አፍታ አይዘንጋ ይታወቅ ምፅጧፉ ።
ወገኔ እየውማ ፤
በወንዟ ሳንደረጅ በአፈሯ ላንወዛ በአየሯ ሳንለማ
በጉልተኛ ኮቴ ዘወትር ስንረገጥ ዘውትር ስንደማ
በሲዖ በእርቦ ሥጋችን ሲዳቀቅ ቀልባችን ሲዘራ
በከበርቴ ገብያ አንሶ ሲመነዘር ወዛችን አንጡራ
ምን ትባሏ ፀሐይ
ምን የሚሏት ብርሃን አንዷት ዘገ ጮራ
ከኛይቱ ጐጆ ከደሳሳ ቀሳ ገባች በወር ተራ ? !

(በድርብ—የወንድና የሴት ድምፅ)

እንደዚህ ከተዋጥህ በትዝታ ዜማ በእንጉርጉሮ ቃና
በፀይኖችህ እያለፈ ጠፍ ሕይወት ባድማ ያ ሁል መርግ ጫና
እንደምን ነበሬ ?
እንዲያ ስቡር ቅስምህ እንደገና የቀና ደሞ የተንሠራራ
ተፍታቶ እንደፀትህ አብዮትን ያሀል ፈራጅ ዳኛ የጠራ ?

(በድምር — የብዙኃን ድምፅ)

የአብዛኛው ሕይወቴን የጨለማ ታሪክ ቀድመህ ብትጠይቀኝ
እንደረኸኩም ዕድሜው ደሞ እንደጥልቀቱ አጥብቆ እየያዘኝ
አስቆዘመኝ እንጂ ፤ — ብርሃንማ ምዕራፍ ሌላም ታሪክ አለኝ ።
ሌላም ታሪክ አለኝ ፤ ያልጣለው ጨለማ ወይ ቀቢፀ ተስፋ
በእግረሙቱ መጥበቅ በቀንበሩ መክበድ አንገቴም ቢደፋ ።
ቅንጣት የብርሃን ዘር ፤
በልቤ አጕንቁሎ ዝግ ብሎ ሥር ሰዶ እያደር የፋፋ ።
እንደ አንዲት ምስኪን ሴት
እንደ በኸር ወላድ ምጥ እሚያስቃስታት ለሞት የቀረበ ፤
ማንስ አለ እንዲህ
ከጨለማ ወጥቶ ሕይወትን ለማየት ሕይወትን ለማቀፍ
ልቦናው የጓጓ መንፈሱ የተራበ ?
እንደዚሁ ነበሬ የእኔውም ተጋድሎ የእኔውም ተጋትሮ
ፀምጦና ቆሽሎ ደምቶና ገርጥቶ ክስሎ ተኮማትሮ

የቅንጣቲቱን ዘር የዘራቱን ቅንጣት መታደግ ጠንክሮ
ሕይወትን ማለምለም ያንን የሞት ኬላ ገንጣጥሎ ሰብሮ ።
ከበዳው ሲበዛ
ብዝበዛው ሲንዛዛ
ከጨለማ ጥጋት በውስጤ የበቀለች ያቺን ዘሃ ብርሃን
አራግቤያታለሁ
ዙሪያዬን ጨለማ ቀጥቼባታለሁ
የፋኖ ፋናዬም ሁና አይቻታለሁ ።
በጉራዕ ዶጋዓሊ በኩዓቲት መተማ በታላቁም ዐድዋ
በኡጋዴን በማይጨው በሌላውም ሁሉ ያገሬ ክልልዋ
ያችው ወሰው ብርሃን
ባሳደረችብኝ ሱብዓዊ ጀግንነት የደረጀ ወኔ እምነትና አለኝታ
ስደክም አበራታ ፤ ስወድቅም አንሥታ
ሰው — በል ጅርማንጅር
ድንበር — ሰበር መንጋ ደመ —ሰች ተኩላ
በቀጭኑ ·፡1፡ዶ
ተመቶ ተጥኗል በየፈፋው ቀርቷል በየአሸዋው ሁላ ።
ወገኔ ዘመዶ ፤
ያችው ቅንጣት ብርሃን ስንት መንገድ መቷት አንጋዳ
ፈባዳ
በየስንቱ ምዕራፍ በጉም ተጨፍቃ በጭጋግ ተጋርዳ
ግን ሁልጊዜም የትም ከሕልሜ ተሻሽታ ከወዜ ጠጥታ
በኔዎች ለኔዎች አብባና አሽታ
እነሆ በቃን
በዐይኖቻችን ለማየት ደምቃና ተፍካክታ
ቷ ብላ ፡ ፈንድታ ።
ከዛሬን ደረሰች ፍሬዋን ልታድል ከረጢቷን ፈትታ
የሰላምን ዋጋ—የእውነትን ዋጋ—የዕሪናን ዋጋ
ልትሰብክ ልታስተምር ለሰው ልጅ በተርታ
ብራና ያላየው
ወረቀት ያልነካው
ቀለም ያልዳሰሰው
ሐቀኛ ታሪኳን ፤ ዜና ገድሏን ከፍታ ጉባዔ ዘርግታ ።



(በነጠላ — የሴትና የወንድ ድምፅ)

ያገሬ ሥርቶ አደር
ታሪክህ ነው ቅኔ ቅኔህ ነው ታሪክ
እልባት የሌለው መጠን ወይም ልክ ፤
ያም ሆኖ ተቋጨ
በመስከረም ፀሐይ በአብዮት ብሥራት ዜና
የጭለማ ልጆች ታዩ ተገላልጠው በዕርቃን ገመና
ምጽዓት—ትንሣኤ
ዳግም ላይኖራቸው ቢወዱም ባይወዱ
ክወንበርህ ቀርበው ተፈጥመው ሔዱ ።

(በድምር—የብዙኃን ድምፅ)

በሰማያዊ መስከረም ሰማይ
የፈነጠቅሽ አብዮት ፀሐይ
ሉል—ዕንቁጣጣሽ—ሲሳይ ፡
ምን ያህል ዘመን ምዕት ዓመት
ምን ይባል ትግል ምን ጥረት ፡
ፊውዳሊዝምን ያህል ጨለማ
ጨለማን ያህል ጠላት
ገድሎ በድል ለመምጣት ?

(በነጠላ—የሴት ድምፅ)

መስከረም
የብዙሃን ብሩህ ሰማይ
ግዙፍ ደማቅ አደባባይ
አብዮት ዕንቁጣጣሽ—ሲሳይ
ይዘምሩ ዕፅዋትሽ
ይምነሽነሹ ጽጌያትሽ
ከበሮ ይምቱ አምባዎችሽ ፡
ድላቸው ነውና ድልሽ ።
ገድላቸው ነውና ገድልሽ ።

(በነጠላ—የወንድ ድምፅ)

መስከረም ፥

የአዲስ ልደት ውብ ብሩና
የትግል ደመራ ደማቅ ፋና
በአድማሳትሽ ላይ ተግ አለ
ሠፈነ ቀስተ ደመና
የሰውና ሰው ኪዳን ዜና ።
ፅልል ይበል ሥርቶ አደርሽ
እልይ ይበል ብዙኃንሽ
ሕልሙ ነውና ሕልምሽ
ግቡ ነውና ግብሽ ።

(በድርብ—የሴትና ወንድ ድምፅ)

መስከረም ፥

የጭቁን ሕዝብ የቀኑ ቀን
የዘመን ትግሉ ሰመመን
የየዕለት ድሉ የዓመት ትመን ፤
የከርሞሽም ድል ቡቃያ
እንዲበቅል ከዛሬ ጉያ
ወጣት ልጆችሽ ብቅ ይበሉ
ለስምሽ እንግጫ ይነቀሉ
ለክብርሽ አበባ ቀጥፈው
ቃልሽን ቃላቸው ይጣፈው ።
እንደበታቸው ይዘምሩው ።

(በኅብረት—የወጣት ሴቶች ድምፅ)

እበባዬ ሆይ— ለምለም
አበባዬ ሆይ— ለምለም
አብዮት —ለምለም
መስከረም— ለምለም
እንዳንቺ ቆንጆ የለም ።
ባልንጀሮቹ— ቁሙ በአንድነት ቁሙ በተራ



አድኅሮት ወድቆ —ቤት እስከሠራ
ዋልጌነት ቀርቶ—ቤት እስከሠራ
መሃይምነት ፤ ድኅነት ጠፍቶ — ቤት እስከሠራ
በሽታ ሞቶ ቤት እስከሠራ ፤
እሠራለሁኝ—ከቤትም ቤት
ሐቅ ዲሞክራሲ—የመላበት ፤
እሠራለሁኝ—ከቤትም ቤት
ሥርቶ አደሮቹ—'ሚኖሩበት ፥
እሠራለሁኝ—ከቤትም ቤት
ዕውቀት አዱኛ—'ሚገባበት ፤
እሠራለሁኝ—ከቤትም ቤት
ቅኔና ዜማ—'ሚሠፍንበት ...ወዘተ

አበባ ለምለም
መስከረም ለምለም
አብዮት ለምለም
እንዳንቺ ቆንጆ የለም ...ወዘተ

* * *

---

.1973

— ይህ ግጥም ሁለተኛውን የኢሠፓአኮ ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ በተዘጋጀው የኪነጥበባት ውድድር ፥ በሥነ ግጥም ዘርፍ አንደኛ የወጣ ነው ። መዘክሮነቱም ለሀገሬ ቁራጥ አብዮታውያን ይሁንልኝ ።

## በስሙ ሠየማት

መቋጠሩንስ ቆጥሯል የትግል አበጊዳ
በደሙ እየጻፈ በሕይወት ሠሌዳ
ሳያሴ ዓመታት ለረኘርም ዘመናት
ጨሶ እንደ ርጥብ እንጨት ተቀጣጥሎ እንደ እሳት
እንደ ወዙ ልቡን ሳይገብር ለጠላት ።
መቋጠሩንስ ቆጥሯል ፣ ...
ቸል ብሏት አያውቅም
የሕይወትን ፊደል ዳር ሁኖ ዳር ቁሞ
ቃል ኪዳን ነበረው በራሱ ጉባኤ ምሎ ተፈጥሞ
የራሱ ሊያደርጋት ወድቆና ተነሥቶ ሮጦና አዝግሞ ።
ቃልኪዳን ነበረው ፣
የሕይወትን ፊደል ቅንጣትና ዘሯን
እጅግ ለምለም ቡጧን
ወይ ዕውቀት ፍሬዋን ፤
በመንቆር ጣቶቹ ሰቅዞና አፍኖ
የያዛትን ምስጡን ትሉን ትኋትሉን
ከላይዋ አራግፎ አብኖ አትኖ
በወዙ ሊያፋፋት
ፀአምሳሉ ሊቀርፃት እንዲኖራት መቅኖ ፤
እንዲኖራት ጤና ሰላም ብልጽግና
’.ማይታጠፍ ሰንደቅ ከቶ እማይገሥ አርማ
የእምነት ዕፁብ ፋና ።
እነሆም አልቀረ ፣
ቃል ኪዳን ቃል ሁኖ አየነው ሲለማ
ከጨለማ ልጆች ከምስጣምስጥ ትሎች ብርሃንን ሲቀማ
ለትግሉም መዘክር ለድሉ ዋስትና
ለዛች የሕይወት ፊደል
ለዛች የፊደል ዘር



ለዛች የዕውቀት ፍሬ ለውልት ቀረፀና
እውነትን ውበትን ፍቅርን እርነትን በላይዋ ነደፈ
በስሙም ሠየማት ፣
በብሩህ ደም-ቀለም "ሠርቶ አደር" ሲል ጻፈ ።

---

ሰኔ 1973 - የሠርቶ አደር ጋዜጣ ፩ኛ ዓመት በተከበረበት
ወቅት ።

## ምነዋ ባየሁኝ

ምነው ባየሁኝ!
መሬቷን ሰቅስቄ
ዛፏን ተራራዋን ቤቷን ሰዋን ሁሉ
        አንድ ላይ ጠቅልዬ
(ቡብርሃን ፍጥነት በሚምዘገዘግ ዘንግ)
        ወዲያ እንጠልጥዬ
ከሰማያት ጣራ ገፍቼ ሰቅዬ ፤
ምነዋ ባየሁኝ!
ጠፈሩን እንጥፌ
ጓዙን ከዋክብቱን እግሬ ሥር አርግፌ
ቀስተ ደመናውን ፈትቼ በጆቼ
በቀለማት ምስጢር ተደመው ዐይኖቼ ፤
ምነዋ ባየሁኝ!
ምነዋ ባየሁኝ!
    የሩቄን አቅርቤ
    የቅርቤን እርቄ ፥
    ጨረቃ ሰልችታኝ
    ምድሪቱን ናፍቄ ።

* * *

. 1974



## ጋዜጠኛው

ጋዜጠኛው አባ ጆሬ ፤
ኸው ሸጌ—ብር ክንፌ
ካደባባይ እስከ ጓዳ
ከኤውላላ እስካንጋዳ
ከቁር ሐሩር—ከለም ጠፉ
ከሸለቆው ከአፋፉ
ከደፍ ጨረፍ—ከች ከተፋ!
ጋዜጠኛው አባ ዲና ፤
በሺ እግሮች እምትባክር
በሺ ዐይኖች እምትማትር
ማን እንዳንተ — የትም ደራሽ
ምዕራፍ ገሣሽ — ኬላ ደምሳሽ
ከነገር ነገር — ነገር ጨራሽ
ከውጥን ውጥን — ግቡን አሳሽ ፤
ማን እንዳንተ ?
    ስንቱን በዐይኑ የሸለተ
    በትዕዝብቱ የሞገተ
    ማን እንዳንተ ?. . .
ገና ቀርበህ ሳትጨብጠው
ለዐመል ያህል በቃኘኸው
በሩቅ ድምፅህ 'ሚበረየው
ሲቃ ይዞት እሚርደው ፤
ግንባርህን እሚፈራ
የቢክራሲ — የቢግራሲ
አባ አድኃሪ — አባ ሴራ
ምን ያህል ነው
ቡብዕርህ የኰተብከው ?. . .
ጋዜጠኛው አባ ጆሬ ፥
መንቆር ብእርህ ስል ነው ካራ
'ሚንደፍር የአሻጥር የዕድፍ ጋራ
እሚፈታ የአድኃሪን መንጋ ጉራ ፤

እስክትወጣ እውነት ብፅዓት
አንዲት ቅንጣት — እውነት ብሥራት
ቁሻሻውን ጥራጊውን
    በታትንሽው እንደ ዘሃ
ስንቱን እንከን
    ትንቅሳለህ
    ስንቱን ሰሀ ።
ጋዜጠኛው አባ መቻል ፤
በር ቢዘጉ አይመልሱህ
አትቀየም ፊት ቢነሡህ
በመርፌ ዐይን — ሰተት ውልብ
በስቁረቷ — እልም ስልብ
ይቺን ጡልብ — ያቺን ቅንጥብ
ከዚች አፈፍ — ከዚያች ገፈፍ ።
መሠሪ እጁን ሲቃጣብህ
አሉባልታ ሲዘርፍብህ
እምትዳኘው በትዕግሥትህ
በኮክቴል ላይ ሲጮህብህ
ባንድ ጉንጭህ
    ዐረቄዋን — ሳብ ምጥጥ
በሌላኛው
    ቁምነገሯን — ዋጥ ስልቅጥ ።

ፀይኖችህ የጊዜ ዐይኖች
ዝንተዓለም ክፍት ግዙፍ በሮች
ጆሮዎችህ እንደ አንቴና
የከበሮ ስስ ብራና ፤
ጋዜጠኛው ፤. . .

---

.1974

እውነትን ለሚፈለፍሉ ንቁ ጋዜጠኞች



# ትዝታ—ከበሮ

ተንተርክኮ እሳቱ ነበልባሉ ኦብቦ
ኑ ደርቡት ሲለን ጃዌውን አቅርቦ
የኔና ያንቺ ልብ ሙቀት — ከላ ኖር ፤
ይኸው የተረፈን ፤—
ቁርና እንጉርጉሮ ፤ ዐመድና እሮሮ

ምቱ ውል የሌለው ትዝታ — ከበሮ ፦

* * *

---

.1975

# ፍቅርና ቀግባር (አንድ ቅንጣት አበባ)

ስንቱ ነገሩ ቀርቶ ፥—
ውብት ደግነትሽ ትዝታው አፍጅቶ
ደርቆና ገርጥቶ
በጥላቻ ደለል
ፀቅያሜ ዳዋ እያደር ተበልቶ
እያደረ ጠፍቶ ፤
አንድ ነገር ብቻ
አለ አንድ ነገር ከኔ ዘንድ የቀፈ
ባይኖቹ ማዕዘን እንባ እያስቋጠረ
ፀሩቅ ዘመን ልቤ ዛሬን እየዋለ
ዛሬን እያደረ ።
በዚያች መጢቅ ሰዓት ፥—
ስሜታችን ባብቶ በፍቅር እምቢልታ
በተግባሬም ጥሪ መልከት ግምግምታ
አንቺና ግዳጄ
ግዳጄና አንቺ ከፍላችሁት ልቤን
ሁለት ሁለት ቦታ ፤
በዚያ ሙስቀለኛ መንገድ ላይ እንደ ቆምሁ
ሳስብ ሳመነታ ፤
ቀጥፌሽ የሰጠሽኝ
በለጋ ጣቶችሽ ያች ቅንጣት አበባ
በተግባሬ አለኝታ በግዳጄ ተስፋ
ፍሬ እንድገነባ
ከቶ አትረሳኝም በክረምት በበጋ
በነጋ በጠባ ።
ለካስ አይደለችም
ቅንጣቲቱ አበባ
ጠፊና ፈጋፊ የቅጠል ወለባ ፥
የዛሬ ውበት ድምቀት
ግን የክርሞ ትቢያ የነገ ገለባ ።
ይልቅስ ሕያው ፍት



አንዳች የፍቅር ዐዋይ የተግባር ጥሪትሽ
ከቶ እማትሟሽሽ
በልቤ የጸደቀች ቋሚ ሐውልትሽ
ልወገኔ ፍሬ ሳንቸ መታሰቢያሽ ።

* * *

---

.1976

# እይ ጀኒ አይ ጀሊ

እይ ጀኒ አይ ጀሊ
የገበያው ጭምት ፣ የቤተክስያን ጡሊ
ብኸር ቅዝዝ በአራዳ ፣ ፍዝ ድንግዝ ፀሜና
ሸር ብሬ በማጀት ፣ ሸው እልም በጓዳ
ውትርትር በአውላላ ፣ ፍስ እብስ ባንፃዳ
ብቅ ጥልቅ
ጥልቅ ብቅ በጉም ጭጋግ አምባ
—እየሩን ሰንጥቆ—
አሜሪካን ሊደርስ አውሮፓ ሊገባ
(ከብሔረ አፍርንጅ ፣)
በሐበሻ ምድር ዘመድ እርም ብሎ
እዚያ ጡት ሊጣባ !
አይ ጀኒ አይ ጀሊ
ሰው ለምን ያማዋል ?
ባህል አፍራሽ ብሎ ይህን ጀሊ ጀኒ
ቅጠል በልቶ እሚውል
ፅዕ አሽቶ እሚያድር እሱ እንደሁ መናኒ
አባ ሆይ ተብዬ
ልከበር አላለ አልተመጻደቀ
'ሰምዓኒ ' እያለ
ጧት ማታ በስግደት ቅስሙ እየደቀቀ
ወገቡ እያለቀ ።
አይ ጀኒ አይ ጀሊ
ዕድሩን ርቆ
ውጣ ውረዱን ንቆ ሲገባ ሱባዔ
ከብቻ ጉባዔ
ይታየዋል ዓለም
ሥያሜ ያላገኘ ያላወቀው ካርታ
ኅብሩ የተለየ
ከምድራችን ባህል ልምድና ገመታ ፤-
ጽጌረዳ ዥማ ወርቅማ ጭልፊቶች
ለማያዊ ላሞች



ክንፍ አልባ እናስር ፣ ጥርስ አልባ ዝሆኖች
ተንፏቃቂ አዕዋፍ ፣ በራሪ ኤሊዎች
ቀንዳቸው የሾለ ገጸ ስብእ ፍጡሮች
ፀዐይናቸው እሚበሉ የጠይብ ዝርዮች
ውሉደ አሣማዎች ።

ይታየዋል ዓለም !...
ብሔረ አንክሮ የድማሜ ጉራ
ጭቅር ሚያሼትበት ቀድሞ ሳይዘራ
ባንድ እሚውሉበት
እባብ ከእርግብ ጫጩት ከሲላ
ኩታራ ከገዲ እባግዕ ከተኩላ ።
ሌላም አለ ብዙ እሚገለጽ ለሱ
እሚሰማው እሱ
እንደ ባዕድ አካል
ተገንጥሎ ሲሔድ ራሱ ከራሱ
እጆቹ እያጠሩ
እቅፉት ሲቸገር መዳበስ ማበሱ
እያደገ ሔዶ
የገዛ አፍንጫው ይላጋል ከአድማሱ !
ወንዙን ገመገሙን
እመር ብለው ሲያልፉ ዳንዴዎቹ እግሮቹ
ላንዲት ቀጭን በይ ግን
ይጨነቅ መንፈሱ ይተማሠር ወርቹ ፤
እየተለጠጠ
ደግሞ እየገዘፈ ጡንቻው የደረቱ
ይዘጋል ትራፊክ
የመኪና መንጋ ያቆማል ከእስፋልቱ !
ጆሮው እየሰላ ይሰማዋል ጉልቶ
የንብሳት ሲጥሲጥታ
የጣዝማ ኩርፍታ
በሣቅን ሙሉግ ያለ—
የሾማና የቄል ጭልሚያና ቱማታ !
ደግሞም ፀሰማይ ቤት —
የመላእክቱና የእጋንንቱ ተረብ አቸኮለሌ ጋሌታ

እየሩን የመላው
የጸጥታው ጩኸት የጩኸቱ ጸጥታ ።
ሲታገል ይታያል
በየሲጃራው ጭስ
በየጭሱ ክበሽ በመርፌ ቀዳዳ
አሾልኮ ራሱን ለመፎጥ ሲዳዳ ፤
ምላሱ ያጣጥማል
ጥርሶቹ ያደቃሉ የነፋስ ጭብጦ
ይክፋል ተራራ
ያፈርሳል ተራራ ፀቅጽበት ተመስጦ
በዕፀ ፋርስ ፈረስ
አንዴ ከጋለበ ከሔደ ሽምጦ ።
አይ ጆኒ አይ ጆሲ.
ይጋልብ እንጂ ታዲያ
በዕፀ ፋርስ ፈረስ እንዳሻው ተቀምጦ
እለበት በተራው ፤
ኮርቻ ደልድሎ እሚጋልብበት ወገቡን እጉብጦ
እንዳች የዛር ወላጅ
(እስከስሙ ዱካክ)
'ምሴን ምሴን' እሚል ዐይኑን አሰፈጥጦ
ፀረፋ አስደፍቶ
ቀልቡን አስጠፍቶ ቅስሙን ደፈጣጦ ።
ሚሚ—ቲቲ—ጁሊ ፣ እኒ — ቤቲ — ቁዚ
ጠይሚቱ ሮዚ
—የዘመኑ ጻድቃን—
ጊዜያቸውን ቸረው ልባቸውን ሰጥተው
በዲስኮ ደስቀው በሮክ ተራኩተው
በብሉስ ለስልሰው. . .ለስልሰው. . .ለስልሰው
ከደረታቸው ውስጥ—
በትረሎሚ አውጥተው — አውተው — አውተው
አዋጥተው — አዋጥተው
በእጆቹ አስጨፍልቀው በድዱ አስጨምቀው
ካላስተናገዱት ወይ ካላባበሉት ፤
ከቶም በጄ አይል



ከቶም አይባበል ጆኒን ከመግረፉ ፤
ይፀልጥ ከማማቀቅ ወይ ከማስጨነቁ
እሱ እሳት ጐርሶ
የኮሾ ሲጃራ እንቅብ ሙሉ ዐመድ
ቁልቁል በጕሮሮው መሸቅሸቅ ማጨቁ !

ጆኒ ነው ጋላቢ — ቀጋላቢ ጌኛ
ጆኒ ምስኪን ፈረስ — ብርቱ ፈረሰኛ
የት ይሆን ድንበርህ
የመድረሻህ አቅጣጫ?
የግልቢያህ አድማሱ ፣ የጉዞህ መቋረጫ ?

* * *

.1976

# ያቺን ሟች ቀን

ጊዜ ሆይ
ሕያው ጊዜ ሆይ
በማይሞተው ገጽህ ላይ
የወጣችን ያቺን ቀን
ያቺን—
የነቀርሻ እባጭ መሣይ
የመርዝ ከረጢት ሥራይ
ሥሯን በርብረህ ንቀል
ዕጢን ፈልገህ ግደል ።
ትብነን
ምትክ አይኑራት አምሳያ ፤
ትምከን
ወራሽ አይኑራት ዝርያ ፤
የሰውን ልጅ ብሩህ ጉዞ
የሰውን ልጅ ደማቅ ዕጣ
በጥላዋ ሳታዳፍን ፥ በግንባሯ ሳታነጣ ።

በሽፏ ሳትቀጭ ቀርታ
ሰፍታ ከሔደች ደርጅታ
ከፅንሷ ሳትወድቅ ተመታ
ገዝፋ ከመጣች ጉልብታ ፤
የሰዎችን ሕሊና አንቃ
በአጋቦስ እጆች ፈጥርቃ
እኩዩ ትዝታን አንቅታ
ትላንት እትራቱን ከፍታ
    የተኙ ትሎች አህይውታ
የሰውን ልጅ አንድ ተስፋ አንድ አልኝታ
በቅዠት እንዳትይዘው ተስፋፍታ ።
በቅዠት እንዳትይዘው
    በቡከንቨልድ መሰል ጉፉ
        በኦዝቪትዝ እሌፍ ኤኬፉ ።



ጊዜ ሆይ
ሕያው ጊዜ ሆይ ፥
    በሻቲላና በሳብራ
    የወጣችን ጨረር ፍራ ፤
    እንደቧም ጽልመት የለ
ብርሃንን ተመስሎ ብርሃንን ያከሰለ ።

* * *

---

.1976
በሣብራና በሻቲላ ለወደቁ ፍልስጥኤማውያን ።

# ጉዟችን

ሩቅ ነው ጉዟችን ፥. . .
ከቶ እማይመጠን
በሚትሮች ጥቅል በአምባዎች ድምር
በኬላዎች ቁጥር ፥
አጣርሶ እሚያልፍ ነው
የዘመንን ቀመር የጊዜንም ስፍር ፤
አቋርጦ እሚሔድ ነው
የራስን ማንነት ሰብእናም ጭምር ።

ድንቅም ነው ጉዟችን ፤
ከኛው እሚጀምር
በኛው እሚጀምር ሃሌታ ምዕራፉ
ከወገን እስኪ.ዘልቅ ከትልማችን ጫፉ ።
ከዓቢይ ግብ — ጠረፉ ።
ውል — አልቦ ሕይወትን መሣይ አሚከላ
ንፉግ አተያይን የመሰለ አሽክላ
እኛው ከእኛው
በእኛው ተመላልሶ ሳንነቅል ሳንከላ ፤
ትልቁ ጉዟችን ከቶ አይሠምርምና
ምን አይፈይድና
እኛው ነን መንገዱ የመነሻው ኬላ ።
ይህ ፍቱን ጉዟችን
ቀርጾና አዘጋጅቶን በብርቱ ሰብእና
በደደረ ፍቃድ በብሩህ ልቦና
አግዝፎ ያሳየናል
የሕዝብን ሙስና
የወገን ድቀቱን መከራ ፈተና
በሚንቃው የወደቀን ተፈጥሮአዊ ጫና
የልንት ምዕታቱን የበከ ሕይወት ዳና ።

አቅርቦ ያሳየናል
ትግላችን – ስፋቱን
ተስፋችን — ጥልቀቱን



የታሪክን ዳፈን የመከፈሉን ኩብደት
ክቡር መሥዋዕትነት ።
ቃልም ያስገባናል ፥—
እጃችንን ጭና ከአልባሌ ቀማ
ረኃብ ድንቁርና ሌላም ሁሉ አበሳ
በወገን ላይ ላይገን ኬህ ከቶ ሳይደራ
በእጅና በአዕምሮ
ሊመተር ሊቆረጥ — በትግል በሥራ ።

የየወቅቱን አድማስ ያልፋል ዘመቻችን
ሩቅ ነው ጉዟችን ፤
አንድም በማለዳ አንድም በበገበግ
አንድም በተጥለግለግ
በፃ ዕይ በበረድ ፥ ወይም በጀንጀግ ፥
ግን መቼም — በየትም
በአብዮታዊ ኮከብ በሕዝባዊ ፈለግ
በሀገር ፍቅር ሐረግ
በድል ፍኖት ጠገግ ።. . .
ሩቅ ነው ጉዟችን
ድንቅም ነው ጉዟችን ።

* * *

---

.ሐምሌ —1977
ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ፥ በመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ላይ ተሠማር
ተው ለነበሩ ምሁራን ።

# እንደግ እንደ ዛፍ

ጥቁር አፈር ዐቅፎን
ጥቁር ብርሃን ውጦን
ሥራ ሥር እንቁለን
        አዝምተን እንደ ሐረግ ፤
ውስጡን ዕመቃቱን
    ጉራንጉሩን ጠገግ ፤
ጭረንና አሽተን
        እንደ ፋና ሶለግ ፤
እንንቀስ አልሚውን
እንልቀም መልካሙን
        እንደ ልባም ሰው ወግ ።
ክፍ ብለን እንድናኝ
        አየሩን ልንመላ
ወደፊት ለመሮጥ እንሒድ ወደኋላ
እንደግ እንደ ዛፍ ዋርካ እንሁን ሾላ ።

* * *

.1978